

# ኢየሩሳሌም በክረምት በበረዶ ተሸፍና::

ሕንፃ አናት ላይ ስለሆነና እንዲሁም ወደ ጎልጎታ መተላለፊያም ስለሆነ ከአለም ላይ የሚጎርፈው ክርስቲያን የሚያልፈው በጎጆዎቹ መሀልና በተሰነጠቀው ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው::

ለምሳሌ በ2000 እ.አ.አ. ወደ 2,672,000 ጎብኚዎች ወደ እስራኤል ሲመጡ አብዛኛዎቹ በዚሁ ቦታ ነው ያለፉት::

ያልታደሱና ሊፈርሱ የተቃረቡ የኢትዮጵያን መነኩሴዎች ጎጆዎች ካማረው የአካባቢው ሕንፃዎች ጋር ሲወዳደሩ ለሚመለከትና ስለ ቦታው ችግር ለማያውቅ ሀገር ጎብኚ፣ ለምንድነው ኢትዮ-ጵያውያን ይህን ቅዱስ ቦታ የሚያበላሹት ብሎ ማሰቡ አይቀርም::

ይህ ቦታ ኢትዮጵያን እንዳሁኑ በረሀብ ብቻ የምትታወቅ ሀገር ሳትሆን በአንድ ወቅት በኢኮኖሚና በሃይማኖት (በኦሪትና በክርስትና) ቀደምትነት እንዳላት ከማስተዋወቅ ፋንታ ኢትዮጵያን በማይሆን ሁኔታ እያስተዋወቀ ነው::



ለምንድነው ዴርሡልጣን ለኢትዮጵያውያኖች የሚገባው?

ካሉት በርካታ ምክንያቶች መሀል አንዱ:- ከጥንት ጀምሮ ኢትዮ-ጵያውያን መነኮሳት ስለነበሩበት፣ ታሪካዊ ቦታቸውና መብታቸው ስለሆነ::

ሁለተኛ:- አሁን ቅዱሳን ቦታዎች የሚተዳደሩበት ለ1878 እ.አ.አ *ስታተስ ኮ* መሰረት የሆነው፣ የ1852 እ.አ.አ *ስታተስ ኮ* ከመውጣቱ በፊት እዚህ ቦታ ስለሚኖሩና በዚሁ ደንብ *መሠረት* ይህ ቦታ ስለሚገባቸው ነው::

አሁን ድረስ የቆየው የኢትዮጵያውያን በቅድስት ሃገር ቆይታ-*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መጻሕፍት መሰረት*-ከጥንት ከሳባና ከሰለሞን ጊዜ በፊት ጀምሮ፣ ሳባውያን ከደቡብ አረቢያ እስከ ሞሶፖታሚያ ያለውን የንግድ መስመር በሚቆጣጠሩበት ዘመን እንደተጀመረ ታሪክ ያስረዳል::

> *"… Solomon was also interested in the overland trade in the south. The visit of the Queen of Sheba (I kings IV1-10, 13) an incident by no means to be dismissed as legendary, it is to be understood in this light.*
>
> *The Sabeans, originally nomadic, had by this time settled and established a kingdom the center of which was in what is today eastern Yemen. Their strategic position as tied to caravan routes from Hadhramant northward toward Palestine and Mesopotamia enabled them to dominate the trade in spice and incense for which the southwestern Arabia was famous. The Queen of Shebas's visit is, therefore, intelligent.*[7]

ከክርስቶስ ልደት በኋላም ኢትዮጵያውያን ወደ ቅድስት ሀገር ይመጡ እንደነበር መፅሐፍ ቅዱስ ያስረዳል::

> *እነሆም፥ ህነደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጀንደረባ የነበረ በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር።*

ጎልጎታ ቤተክርስቲያን በተሰራ ጊዜም በኮንስታንቲንና በእናቱ ትዛዝ በኢየሩሳሌም የነበረው ቅዱሳት መካናት ርስት እንደ ቀድሞው እንደ ቀድሞው ለኢትዮጵያውያን እንደተመለሰ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መፃህፍት ያስረዳሉ። [8]

ከ386-412 እ.እ.አ. ቤተልሔም ውስጥ የነበረው የቅዱስ ጀሮሜ ተከታዮች በነበሩት በፓውላና በልጂ የተፃፉ ሁለት ደብዳቤዎች፣ የኢትዮጵያውያንን ወደ ቅድስት ሀገር መምጣት ያገልፃሉ።

ኢትዮጵያውያኖች እነዚህ ቦታዎች ሲኖሩ ያዩ አስተዳደሮች፥ ከተለያዩ እስም ክፍል የመጡ ተሳሳሚዎች የፃፏቸው የግል ማስታወሻዎች፥ ሌሎች ቤተክርስቲያኖች የፃፏቸው ፅሁፎችና አውሮፓውያን እጅ ገብተው የነበሩ በኢትዮጵያውያን የተፃፉ ፅሁፎች፣ በአሁን ሰአት ለኢትዮጵያውያን እንደትልቅ ማስረጃዎች ናቸው።

ለምሳሌ:- ኢትዮጵያውያን በዴርሡልጣን እንደነበሩ ከሚገልፁ ፅሁፎች መሀል ኢየሩሳሌምን በ638 እ.ኤ.አ. የያዘው የኦመር ኢቢን አልክታብ ትዛዝ፥ በ1517 እ.ኤ.አ. ኢየሩሳሌምን የያዘው የኦቶማን ቱርክ ሱልጣን ሳሊም ያወጣው ትእዛዝና ከሱ ቀጥሎ ይህንኑ ትእዛዝ በ1550 እ.ኤ.አ. ያፀደቀው የኦቶማን ቱርክ ሱልጣን ሱሌይማን ያወጣው ትእዛዝ ሲሆኑ።[5]

ሁለተኛ ኢትዮጵያውያን መነኩሴዎች ዴርሡልጣን ውስጥ እንደነበሩ:-
“ . . . አብረሐም ይስሐቅን ሊሰዋ የነበረበት ቦታ ላይ አበሾች ቤተክርስቲያን አላቸው . . . ”

በማለት ቅድስት ሀገርን በ1532 እ.ኤ.አ. ተሳልሞ የነበረው ፈረንሳዊው ቻርልስ ፍሊፔ (Charles Philippe de



Chəpmpermoy et de Grandchəmp) የፃፈው አንዱ ማስረጃ ነው።[5]

ሶስተኛ “የቅድስት ሀገር ማሕደር” (1631-1647 እ.ኤ.አ.) በሚሰው መፅሐፉ ውስጥ ፍራንሲስካን የሚባሉ ክርስቲያኖች ሀላፊ የነበረው ፍራንቼስኮ ዲ ቬርኒኤር፣ ኢትዮጵያኖች ዴርሡልጣን ውስጥ እንደነበሩ መስክሯል።[5]

ባጭሩ ዴርሡልጣን ለኢትዮጵያውያኖች የሚገባው ታሪካዊ መብታቸው ስለሆነና ስታተስ ኮ ስለ ሰሚፈቅድላቸው ነው።

ይህንን ሃስብ የሚደግፍ አስተያየት ሄግ በሚገኘው የታወቀው አለም አቀፍ ፍርድ ቤት አባልና የአለም አቀፍ ፍርድ ተቋም አባል በነበረው፣ በፔትሮ ግራድ የአለም አቀፍ ሕግ ፕሮፌሰር በነበረው በባሮን ኖልድ ቀረቧል።

ፕሮፌሰር ባሮን ኖልድ እዚህ ታሪክ ውስጥ የገባው በሩሲያዊው ልዑል ምክንያት ነው።

በ1896 እ.አ.አ. በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ኒኮላስ ሌድቬሬ ከሩሳያ ልኡካን ቡድን ጋር ኢትዮጵያ በመጣበት ጊዜ ወርቅ እንዲፈስግ ፈቃድ ይጠይቅና ፈቃድ ያገኛል። ነገር ግን የፈለገበት ቦታ ወርቅ ሳያገኝ ይቀራል።

በ1905 እ.አ.አ. ኒኮላስ ሌድቬሬ እስክንድርያ (ግብፅ) ውስጥ ኢየሩሳሌም ያለውን የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ጉዳይ ከሚከታተል ልእካን ቡድን ጋር ይገናኛል። ከዚያም የዳግማዊ ምኒልክን በጎ ፈቃድ ለማግኘት ሲል በዴርሡልጣን ጉዳይ ኢትዮጵያን ለመርዳት ይወስንና በኦቶማን ቱርክ ማህደሮች ውስጥ ስለ ለኢትዮጵያ ባለቤትነት ማስረጃ ያፈላልጋል። ከዚያም ለኢትዮጵያ የሚጠቅሙ በርካታ ማስረጃዎችና ትእዛዞች አገኘ።

በ1914 እ.አ.አ. ሩስያ የተገኙትን የመዝገብ ማስረጃዎች ለኢትዮጵያ ከመስጠቷ በፊት ቅድመ ግዴታ ጠይቃለች። ያም ከ12 የክርስትና ቅዱስ ቦታዎች ሁለቱ ለሩስያ እንዲሆን የሚል ነበር። በዚህም ላይ ስምምነት ተደርሶ በፊርማ ሊፀድቅ ሲል አንደኛው አለም ጦርነት ይጀመርና የሩስያ ልኡካን ቡድን አዲስ አበባ ሳይደርስ ቀረ።

ጦርነቱ ሲያበቃም ሩሲያ ውስጥ "አብዮት ፈንድቶ" ስለነበረ ስምምነቱ ሳይፀድቅ ቀረ።

በኋላ ላይም መዛግብቶቹ የሩስያው ልዑል *አሌክሲስ ሚካኤሎቪች* እጅ ይደረሱና እሱም ለፕሮፌሰር *ባሮን ኖልድ* በ1924 እ.እ.አ አስረከበው።

ፕሮፌስር *ባሮን ኖልድ*- 16 ገፆች በሚሆነው አስተያየቱ ቅድስት ሀገርን የጎበኙ የበርካታ ጎብኚዎች ማስታወሳቸንና በ1878 እ.አ.አ. በርሲን ላይ እለም አቀፍ እውቅና ያገኘውን *ስታተስ ኮ* ደንበ ተመርኩዞ፣ የኢትዮጵያውያንን የብዙ ዘመናት በዴርሡልጣን መብት አረጋግጧል።[5]

በሰኔ 1925 አ.እ.አ. እዲስ አበባን የጎበኘው ሩሲያዊው ልዑል *አሌክሲስ ሚካሎቪች* የፕሮፌሰር *ባሮን ኖልድን* አስተያየት ለኢትዮጵያ *መንግስት* አቅርቧል።

በእነዚህ ምክንያቶች ዴርሡልጣን ለኢትዮጵያውያ የሚገባ ቢሆንም ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችና የሚመለከታቸው የመንግስት ባለስልጣናት በዴርሡልጣን ላይ ያለውን መብት ለማስከበር በቂ ጥረት እስካላደረጉ ድረስ፣ ያሉትን መብቶች

በመጥቀስ ብቻ ዴርሡልጣን ሙሉ ለሙሉ የኢትዮጵያውያን አይሆንም።

ለኢትዮጵያውያን የሚገባ ከሆነ ለምንድነው ያሉትን ማደስና አዲስ መገንባት የማይችሉት?

ዋናው ምክንያት የሚመለከታቸው የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣኖችና ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የዴርሡልጣንን ችግር ለመፍታት አስፈላጊውን ያህል ክትትልና በቂ ጥረት እለማድረግ ናቸው።

በእስራኤል የኢትዮጵያ ኤምባሲ አንደኛ ፀሀፊ የሆኑትን ባለስልጣን፣ ለምን የኢትዮጵያ መንግስት የዴርሡልጣንን ችግር ለመፍታት ጥረት አያደርግም ስንላቸው።



*መልሳቸው:- መንግስት የሚያደርጋቸውን ጥረቶች ሁሉ ስለማያስተዋውቅና እኛ ስለማናውቅ እንጂ መንግስት ችግሮቹን ለመፍታት እየጣረ ነው ብለውናል።*

እንደሚባለው ጥረትና እንቅስቃሴ ከተደረገ ዴርሡልጣን ውስጥና የቀሩት የኢትዮጵያ ቦታዎች ላይ ለምን ትንሽ እንኳን ለወጥ አይታይም ስንላቸው። አጥጋቢ መልስ አልሰጡንም።

በተጨማሪ በኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ ከፍተኛ የኢትዮጵያ ልኡካን ቡድን ከሰኔ 1-3/2004 እ.አ.እ. (ከግንቦት 24-26/1996 ዓ.ም.) የሶስት ቀን የስራ ጉብኝት ለማድረግ ኢየሩሳሌም መጥቶ፣ ዴርሡልጣን ውስጥ ያሉትን ችግሮችና የቀሩትን ቦታዎች ሳይመለከት እንዴት ሄደ ስንላቸው።

*ለደህንነታቸው ስለሚያሰጋ ዴርሡልጣንን ሊጎበኙ አልቻሉም ብለውናል።*

ስንት ኢትዮጵያውያን ደማቸውን ያፈሰሱበትና አሁንም እየተቸገሩ ያሉበትን፥ የኢትዮጵያን ስም በማይሆን መልኩ እያስተዋወቀ ያለውንና ኢትዮጵያን ከክርስትና፥ ከመፅሐፍ ቅዱስና ከፅዮን ጋር የነበራትን ግንኙነት ለመወከል ቀድሞ ከነበሩት ቦታዎች የተረፈውን የመጨረሻ ቦታ ዴርሡልጣንን፣ ምን እንደሚመስል እንኳን ሳይጎበኙ ደብረገነት ገዳም ብቻ ደርሰው ነው የሄዱት።
ይሄም ሁኔታ ዴርሡልጣን ያሉትን መነኮሳት ምን ያህል እንዳናደዳቸውና ሞራላቸውን እንደነካው ቀርቦ ያነጋገራቸው ብቻ ነው የሚረዳው።

በጉብኝቱ ወቅት ንጉሥ ዳዎት ሆቴል ድረስ ሄደው ላናገሯቸው ለገዳማቱ ማህበር ሀላፊዎች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከእስራኤል ባለስልጣናት ጋር ስለ ዴርሡልጣን ገዳም ተነጋግረው እንደነበረና የእስራኤል ባለስልጣናት ዴርሡልጣንን ሊያስተካክሉት ቃል እንደገቡላቸው ቢገልፁም፣ ከጉብኝቱ በኋላ ምንም ለውጥ አለመኖሩና ዴርሡልጣን በየቀኑ እየተበላሸ መሄድ የሚመለከታቸው የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት በቂ ትኩረት እንዳልሰጡትና በቂ ጥረት እያደረጉ እንዳልሆነ ማስረጃ ነው።

በምእመናንም በኩል ቢሆን፣ ዴርሡልጣን ውስጥ ደርሶ በነበረው በኮፕት መነኮሳትና ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ግጭት ምክንያት

አሜርካን ሀገር (ዩናይትድ ስቴትስ) በሚገኙ ኢትዮጵያውያን በ2002 እ.አ.አ. ተደርገው ከነበሩት እንቅስቃሴዎች ሌላ ከዚያ ወዲህ ምንም አይነት ዴርሡልጣንን ለማሻሻል የተደረገ ጥረት አልታየም።

ኢትዮጵያና አሜሪካ ውስጥ ተጀምሮ የነበረው ስለ ዴርሡልጣን እንቅስቃሴ ለዚህ ችግር መፍትሄ ለማግኘት ጠቃሚ ቢሆንም በቀጣይነት ስላልተደረገ ለውጥ እስካሁን አልታየም።

በተለይ በአሁን ሰአት ችግር ላይ ያሉት የኢትዮጵያ መነኮሳት እየሆኑ ከግብጾች ይልቅ የሚመስከታቸው የኢትዮጵያ መንግስት ተወካዮችና በተለያዩ የአለም ክፍል ያሉ ኢትዮጵያውያን የዲፕሎማሲና የሕግ ባለሞያዎች መፍትሄውን ለማፈላለግ አለመሞከር የሚገርም ነው።

አማራጭ መፍትሄዎች፡- አንደኛ- ቀድሞውንም ቦታው የኢትዮጵያ እንደነበር የሚያሳዩ የተሟሉ ለፍርድ ቤት የሚሆኑ ማስረጃዎች ይዞና ለእሥራኤል መንግስት አቅርቦ ዴርሡልጣንን ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ማድረግ ነው።

ዴርሡልጣን ውስጥ ያሉት ማስረጃዎች በኮፕቶች በ1838 እ.አ.አ. ስለተቃጠሉ አሁን የተሟሉ ለፍርድ ቤት የሚሆኑ ማስረጃዎች ከሌሎች ቦታዎች ማስባሰብ ያስፈልጋል።

ማስረጃዎች የሚባሉት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና ሎሌች ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ደብዳቤዎች። ኢየሩሳሌምን ያስተዳደሩ ኃይሎች ለምሳሌ፡- *የኦቶማን ቱርክ* አስተዳደር፥ *የመምሉክስ* አስተዳደር፥ *የአዩባዊ* አስተዳደር፥ *የፋጡማዊ* አስተዳደር፥ *የአባሳዊ* አስተዳደር፥ *የመስቀላውያን* አስተዳደር፥ *የኡመያይድ* አስተዳደር፥ *የቢዛንቲን* አስተዳደርና የሌሎች አስተዳደሮች የግብር ደረሰኞች የመሳሰሉ ማስረጃዎች ናቸው።

እንዲሁም የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ለምሳሌ፡- የግሪክ ኦርቶዶክስ፥ የሮም ካቶሊክ፥ ፍራንሲካኖች ማህደሮች፣ እንዲሁም የቅድስት ሀገር ተሳላሚዎች ማስታወሻዎች ናቸው።



ማስረጃዎች ማሰባሰብ በመንግስት አካል ወይም በድርጅት ብቻ ሳይሆን፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የጥናት ጽሁፍ በሚያቀርቡ ምሁራኖች ሊሰበሰብ የሚችል ነው።

ሁለተኛ፡- እነዚህን ማስረጃዎች ማሰባሰብ የሚጠቅመው ለፍርድ ቤት ብቻ ሳይሆን ቀና አመለካከት ካላቸው የኮፕት መነኮሳትና የኮፕት ምእመናን ጋር ስምምነት ለመፍጠር ጭምርም ነው።

ቦታው አሁን *በስታተስ ኮ* ደንብ ስለሚተዳደር ኢትዮጵያውያን ያለ ኮፕቶች ስምምነት ለውጥ ማድረግ የማይችሉትን ያህል፣ ኮፕቶች ኢትዮጵያውያን መነኩሴዎችን ሊያስወጡ አይችሉም። ስለዚህ ለጊዜው በስምምነት ቦታውን ማስተካከል አንዱ አማራጭ ነው።

ከአሁን በፊት እንደታየው ግን ከኮፕት መነኮሳት ጋር በቀጥታ ስምምነት ላይ መድረስ ቀላል አይደለም።

ስምምነት ለማድረግ ማተኮር ያለበት ችግሩን ሊረዱ ከሚችሉ የኮፕት መነኮሳት፥ የኮፕት ምዕመናንና ከአባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ወደ ኢትዮጵያ ከሚመጡ የግብፅ ባለስልጣኖችና ባለሙያዎች ላይ ነው።

በአባይ ወንዝ ምክንያት የኢትዮጵያና የግብፅ ባለስልጣኖችና ባለሙያዎች በተደጋጋሚ የሚገናኙ ሲሆን። ይህንኑ መግባባት ተጠቅሞ ለዴርሱልጣን መፍትሄ መፈለግ አንድ መንገድ ነው።

አባይ ለግብፅ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን የአባይን ግኑኝነት ጫና በማድረግ፣ አሁን ከሚታገሉት መነኩሴዎች ይልቅ ለኢትዮጵያ መንግስትና ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የቀለለ ነው።

> *As a country with an arid landscape, little rain and 97% desert, Egypt is dependant on the Nile River for its existence. The Greek historian Herodatus (c.486-425 B.C.) observed that Egypt is "a gift of the Nile" and today nearly the entire population of Egypt continues to live in the narrow bands of the Nile valley.*

ሶስተኛ አማራጭ መፍትሄ፡- በመግባባትም ሆነ ጫና በማድረግ ይሄንን ጉዳይ ማስተካከል የሚቻለው፣ ለሀገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም ካላመጣ የዴርሡልጣን ጭቅጭቅ ውስጥ መግባት ከማይፈልገው ከእስራኤል መንግስት ጋር ነው።

በኢትዮጵያውያንና እስራኤላውያን መሃል መልካም የሆነ ታሪካዊ፥ ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ግኑኝነት አለ።

የእስራኤል መንግስት ላይ የዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚና የፓለቲካ ጫና በማድረግ *ስታተስ ኮ* በሚፈቅደው መሰረት አዲስ ግንባታ ሆነ እድሳ እንዲያደረግ ጥረት ማድረግ ሌላው አማራጭ ነው። በአሁን ሰአት በርካታ የእስራኤል ኩባንያዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚንቀሳቀሱ፣ ኢትዮጵያ ከቀድሞ የበለጠ ለእስራኤል በኢኮኖሚ ጠቃሚ ሆናለች።

እነኚህን ግኑኝነቶች ምክንያት አድርጎ የእስራኤልን መንግስት ባለ ስልጣኖች ዴርሡልጣንን እንዲጎበኙና እዚያ ውስጥ ያለውን ሽታ፥ የተሰነጠቁ ግርጊዳዎችና እየተቸገሩ ላሉት የኢትዮጵያ መነኮሳት ሰብአዊ እርዳታ እንዲያገኙ ማድረግ ሆነው ብለው ላለቡበት የሚመለከታቸው የኢትዮጵያ መንግስት ተወካዮችና ኢትዮጵያውን ባለሙያዎች አሁን አመቺ ነው።

አንዳንድ ታዛቢዎች ደግሞ ለምን "ሞዓ አንበሳ" ታሪካዊ፥ ሃይማኖታዊና ለለሞናዊ ግንኙነት ተጠቅሞ። ለዚህ ችግር መፍትሄ አፈላልጎ ለኢትዮጵያ ውለታ አይውልም ይላሉ።

"ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" ተብሎ የተፃፈባቸው ሕንፃዎች በሞሉባትና የይሁዳ ግዛት ርዕሰ ከተማ በሆነችው የታወቀ የ"ሞዓ አንበሳ" ቢሮና ተወካይ የለም።

እንዲሁም ከመንግስት ውጪ ያሉት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ለምን መፍትሄ አፈላልገው ውለታ አያስቆጥሩም የሚሉ እስተያየቶችም አሉ።

እስራኤል ባለስልጣኖች አሁን ዴርሡልጣን ለመጠገን ምን እቅድ አላቸው?



የእስራኤል የሃይማኖት ጉዳይ ሚንስቴር መስሪያ ቤት ፈርሶ አሁን በምትኩ ይሄንን ጉዳይ የሚመለከተው በሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስቴር መስሪያ ቤት ስር የክርስቲያን ጉዳዮች ክፍል ነው።

በቅርቡ የዚህ ክፍል ሃላፊ ሆነው የተሾሙትን ሚስተር *ሲዛርን* በ4/11/2004 እ.አ.እ.- አንደኛ የዴርሡልጣን መበላሸት ለእስራኤል የቱሪስት ኢንደስትሪ ጥሩ አይደለም። ሁለተኛ *በስታተስ ኮ* ደንብ ቦታውን እስራኤል የመጠገን ግዴታ አለባት እና ለምንድነው እስራኤል ይህን ቦታ የማታስተካክለው ብለን ስንጠይቃቸው?

በእስራኤል ክኔሴት (ምክር ቤት) የክልላዊ ደህንነት ምክትል ፀሀፊ በሩቪ ጋል የሚመራ ቡድን ቦታውን ጎብኝቶ ለእስራኤል ሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስትር ለእብራሐም *ፖራፅ* ቦታው እንዲጠገን ደብዳቤ በፃፈው መሰረት፣ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስቴር መስሪያ ቤት ስር የሆነው የክርስቲያን ጉዳዮች ክፍል የኤሌክትሪክ መስመርናና የፍሳሽ ማስተላለፊያ መስመሮችን የሚመለከቱ መሃንዲሶች እንደላከ። መሃንዲሶቹ ያቀረቡት ስራው የሚፈጀው የገንዘብና የጊዜ ግምትን የያዘ ሪፖርት አሁን እየተጠና ነው። በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

እስከዛሬ ለምን አላስተካከላችሁም ስንላቸው? *ከዚያ በፊት ስለ ነበረው አላውቅም* ነበር መልሳቸው።

ለምን አሁን ዴርሡልጣንን ችግር ለመፍታት አመቺ ጊዜ ነው?

የዴርሡልጣን ጉዳይ የሚመለከታቸውን የኢትዮጵያ፥ የእስራ-ኤልና የግብፅ፣ እንዲሁም ወደ ፊት ሊመለከተው የሚችለውን የፍልስጥኤምን አስተዳደር ግኑኝነቶች መመልከት ይሄንን ጥያቄ ለመመለስ ይረዳል።

ኢትዮጵያ ከእስራኤል ጋር በአሁን ወቅት ጥሩ የኢኮኖሚና የዲፕሎማሲ ግኑኝነት ስላላት፣ በዚህም የተነሳ በሁለቱ ሀገሮች ባለስልጣኖች፥ በንግድና በሌሎች ባለሙያዎች መሀል የቀረበ ግኑኝነት አለ።

የኢትዮጵያ ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር መስፍን ስዩም እስራኤል ጉብኝተው ከተመለሱ በኋላ፣ የእስራኤል ውጪ ጉዳይ ሚንስትር *በሲልቫን ሸሎም* የተመራ የእስራኤል ከፍተኛ ባለስልጣን ቡድንና

የንግድ ስራ ተወካዮች ኢትዮጵያን በጥር 2004 እ.አ.አ. ከጎበኙ በኋላ፣ በንግድ፥ በኢንቨስትመንት፥ በኢንደስትሪ፥ በግብርና ዘርፎችና በሌሎች ዘርፎች በጋራ ስመስራት አሳውቀዋል።

በተጨማሪ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሚመራ ከፍተኛ የልኡካን ቡድን እስራኤልን ከሰኔ 1-5/2004 እ.አ.አ. ከጎበኘ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሷል። በጉብኝቱ መጨረሻም ጉብኝቱ የተሳካ እንደነበረና ሁለቱ ሀገሮች በኢኮኖሚ፥ በንግድና ባህል፣ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ሽብር ፈጠራን ስመዋጋት መስማማታቸው ተገልጧል።

በአንፃሩ በሙሴ መሪነት ነፃ እስከ ወጡበት ድረስ ግብፅ በስደት የተሰቃዩበት ሀገር ስትሆን፣ አዲሲቱ እስራኤል ከተመሰረተች በኋላ ሶስት ጊዜ ትትልቅ ጦርነቶችን ያስተባበረች ሀገር ናት። በ1948 እ.አ.አ. የነፃነት ጦርነት፥ በ1967 እ.አ.አ. የስድስቱ ቀን ጦርነትና በ1973 እ.አ.አ. *የዮም ኪፑር* ጦርነት።

የእስራኤል ጠቅላይ ሚንስተር በነበሩት *በሚናኬም ቤገንና* የግብፅ *መሪ በአንዋር ሰዳት* ሰላም ከተፈራረሙ በኋላም፣ የግብፅ አስልምና መሪዎችና የግብፅ ዜና ማሰራጫዎች ፀረ-እስራኤል መልክት ነው የሚያስተላልፉት። በ2000 እ.አ.አ በተፋፋመው የፍልስጥኤምና የእስራኤል ግጭት (ኢንቲፋዳ)ና ስልጣን ላይ ባለው *የአርየል ሻሮን* መንግስት ቀድሞ የነበረው "ቀዝቃዛ ሰላም" ወይም "COLD PEACE" ተብሎ የሚጠራው ግንኙነት የባሰውኑ ቀዝቅዞ ነው ያለው።

በ2000 እ.አ.አ ላይ በተፋፋመው ግጭት ምክንያት ግብፅ እስራኤል የነበረውን አምባሳደሯን ከመለሰች ወዲህ እስካሁን እስከ ጥር 2005 እ.አ.አ አልመለሰችም።

በዚህ የግብፅ ዲፕሎማቶች የራቁበት ጊዜ ነገር ግን ኢትዮጵያውያን መሪዎች ከእስራኤል ባለስልጣናት ጋር የተቀራረቡበት ጊዜ፣ ያሄንን አጋጣሚ ተጠቅሞ ዴርሡልጣን ውስጥ የተሰነጠቁ የቤተክርስቲያን ግርጊዳና የፍሳሽ መውረጃ መስመሮችን *የስታተስ ኮ* ደንብ በሚፈቅደው መሰረት የእስራኤል መንግስት እንዲሰራ ማድረግ ጉዳዩን ትኩረት ሰጥቶ ኢትዮጵያውያን ባለስልጣኖች አሁን አመቺ ጊዜ ነው።



በተጨማሪ የግብፅና የኢትዮጵያ መንግስት ተወካዮች የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ይገናኛሉ። ለምሳሌ:- የምስራቅና ደቡብ አፍሪካ የጋራ ገበያ አባል ሀገሮች ናቸው።

እንዲሁም በአባይ ወንዝ ምክንያት የኢትዮጵያና የግብፅ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ይገናኛሉ። ለምሳሌ:- ኬንያ ውስጥ ከመጋቢት 18 እስከ 19 2004 እ.አ.አ. አስራ ሁለተኛው አመታዊ ስብሰባ ሳካሄደው የአባይ *(የናይል ወንዝ)* ተፋሰስ ሀገሮች የሚንስትሮች መማክርት፣ ኢትዮጵያና ግብፅ አባላቶች ናቸው።

በተወካዮች ምክር ቤት የውጪ ጉዳይ፥ መከላከያና ደህንነት ተወካይ ቋሚ ሲቀመንበር በሆኑት በሃይሉ ኪሮስ መሪነት ግብፅን ሰጎበኘው የኢትዮጵያ ልኡካን ቡድን፣ የግብፅ ተወካዮች በኢንቨስትመንት፥ በንግድና በውሀ ሀብት ልማት ከኢትዮጵያ ጋር መስራት እንደሚሹ የግብፅ ተወካዮች አስታውቀዋል።

በተጨማሪ የግብፅ ምክትል ጠቅላይ ሚንስተር ዶ/ር ዮሴፍ ዋሊ 149 ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች በግብርና ሙያ በልገሳ መልክ ማስልጠን እንደምትችል ገልፀዋል።

ይህን ያህል ግንኙነት ከግብፅ ባለስልጣኖች ጋር እያለ፣ ስንት ጭቅጭቅና ደም መፋሰስ እየፈጠረ ያለን ቦታን ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ወጪ ማስተካከል እንዲችሉ ከግብፅ ባለስልጣኖች ወይም ከኮፕቶች ጋር ስምምነት ላይ ለመድረስ አሁን አመቺ ጊዜ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ፍልስጥኤሞች ምስራቅ ኢየሩሳሌም የነሱ አስተዳር ስር እንዲሆን ነው እየታገሉ ያሉት። ምስራቅ ኢየሩሳሌም ማለት ዴርሡልጣንና የኢትዮጵያ ገዳማት ጽሕፈት ቤት ያለበትን ጨምሮ የያዘ የኢየሩሳሌም ክፍል ሲሆን አሁን በእስራኤል አስተዳደር ስር ነው።

የእስራኤል ጠቅላይ ሚንስተር በነበሩት *በኤሁድ ባራክና* በፍልስጥኤሞች *መሪ በያሲር አረፋት* መሀል አሜሪካን ሀገር ውስጥ *የዋይ ስምምነት* ተብሎ በሚታወቀው ስምምነት ወቅት፣ *አረፋት* ብዙ ቦታ ስለፈለጉ ስምምነቱ ባይፈርስ ኖሮ፣ ኤሁድ ባራክ



የመነኮሳቱ ማህበር በዴርሡልጣን::

ምስራቅ ኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉ ቦታዎች ለያሲር አረፋት አስተዳደር ሊሰጡ ተስማምተው እንደ ነበር ይታወቃል::

ወደፊት እነኚህ ቦታዎች በፍልስጥኤሞች አስተዳደር ስር ከሆኑ:: የፍልስጥኤም አስተዳደር "አለቆች" የሚባሉት ግብፆች፣ የፍልስጥኤም አስተዳደር ላይ ጫና አድርገው አሁን ማድረግ ያልቻሉትን ወደፊት ሊያደርጉ እንደሚችሉ መገመት አስቸጋሪ አይደልም::

ዴርሡልጣን በፍልስጥኤም አስተዳደር ስር ከሆነ፣ ዋነኛ ወዳጅ ሆና ከአሜሪካናችና ከእስራኤሎች ጋር ለምትደራደረው ግብፅ (አሁን እንደሚታየው ኢትዮጵያውያን ቦታውን ችላ ማለታቸውን አይተው) ዴርሡልጣንን ለኮፕት ሊሰጡት ይችላሉ::

ከፍልስጥኤሞች ጋር ወዳጅነት ያላቸው የግብፅ መሪዎች ብቻ አይደሉም የኮፕት አባላትም ናቸው:: ለምሳሌ የኮፕት ፓትርያርክ



ሲኖዳ ሶስተኛ፣ "አል ታደሞን" ("AL Tadmon") ለተባለው ጋዜጣ የሰጡት አስተያየትና *"Ha'aretz" 29/6/86* እ.አ.አ. የተባለው የእስራኤል ጋዜጣ የዘገበው ይህንኑ የሚደግፈው ነው::

*"ትልቁ ችግር ዴርሡልጣን አይደለም፣ የፍልስጥኤሞች ችግር ነው" ፤ " ... ኢየሩሳሌም ነፃ እስከምትወጣ ግብፅና ሌላው ዓለም ያሉ ኮፕቶች ኢየሩሳሌምን አይጎበኙም...* " በማለት የሰጡት አስተያየት፣ እኚህ የኮፕት ፓትሪያርክ በፍልስጥኤሞች ዘንድ አስተዋውቋቸው፣ የፍልስጥኤሞችን ድጋፍ አስገኝቶላቸዋል::

ባጭሩ በአሁን ሰአት ለሚመለከታቸው ኢትዮጵያውያንን ባለ-ስልጣኖችና ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ዴርሡልጣንን ለማስተካል አሁን ጥሩ ሁኔታ አለ::

በኮፕቶችና ኢትዮጵያውያን መነኩሴዎች መሀል ያሉት ችግሮች እየተባባሱ ሄደውና ከሌሎች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግሮች ጋር ተደምረው፣ በታሪክና በሃይማኖት ትስስር ባላቸው በሁለቱ አገሮች መሀል ግጭት ሊነሳ ይችላል::

ለምሳሌ በጎልጎታ ቁልፍ የተነሳ *የክሬሚያ* ጦርነት ተደርጎ በርካታ ሰዎች ሞተዋል::

ኢየሩሳሌም ውስጥ ያለውን የጎልጎታ ቤተክርስቲያንን ቁልፍ ለመያዝ የግሪክ ኦርቶዶክስና የሮም ካቶሊክ ክርክር ላይ እንዳሉ፣ በ1847 እ.አ.አ. ቤተልሔም ውስጥ የልደቱ ቤተክርስቲያን ላይ በላቲንኛ (በካቶሊኮች) ተፅፎ የተቀመጠው ኮከብ ሲጠፋ *የክሬሚያ* ጦርነት ተጀመረ::

ከዚያ በፊት ግን የፈረንሳዩ አምባሳደር ካቶሊኮችን ወክሎ እየተከራከረ እያለ፣ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን በመወከልና የተዳከመውን የኦቶማን ቱርክን ግዛቶች ለመቆጣጠር ባለው ፍላጎት የተነሳ የሩሲያው *ዛር (ንጉሥ)* ኒኮላይ አንደኛ የኦቶማን ሱልጣን ቁልፉን ለግሪክ ኦርቶዶክስ እንዲያስረክብ ትእዛዝ ሰጠ:: ሀገሩ ውስጥ በነበሩት ችግሮች ምክንያት የካቶሊክ እምነት ተከታዮችን ድጋፍ ፈልጎ የነበረው የፈረንሳዩ *ሉዊስ ናፖሊዮን* ደግሞ ካቶሊኮችን ወክሎ ቁልፉ ለካቶሊኮች እንዲሰጥ አዘዘ::

በሁለቱ ኃያላን ሀገሮች ትእዛዝ የተቸገረው የኦቶማን ቱርክ ሡልጣን አብዱል መጂድ በበኩሉ *ሰታተስ ኮ* እንዲፀና አስታወቀ::

ሁኔታዎች በዚህ እንዳሉ፣ ከጥቁር ባህር እስከ ሜዲትሬኒያን ባህር ያሰውን የባሕር መስመር ሩሲያ በዚህ አጋጣሚ ልትቆጣጠር ትችላለች ብላ የሰጋችው ብሪታንያ፣ ሰፈረንሳይ ትብብሯን ገለፀች:: በፈረንሳይና በብሪታንያ የተመካው የኦቶማን ሡልጣን የሩሲያን ትዛዝ ችላ ሲል፣ ሩሲያ የቱርክን መርከቦች በ1855 እ.ኤ.አ. ታጠፋና የኦቶማን ግዛት የነበረውንና አውሮፓ ውስጥ የነበረውን የዳኑብ ክልል ወረረች::

በአፀፋውም የኦቶማን ቱርክ፥ የፈረንሳይና የብሪታንያ ሕብረት ጦር *ክሬሚያና ሰቫስቶፓል* የሚባሉ የሩሲያን ግዛቶች አጠቁ:: አንድ አመት አካባቢ በፈጀውና በዚህ የ*ክሬሚያ* ጦርነት በመባል የሚታወቀው ጦርነት ሲያበቃ ከሁሉም ወገን በድምሩ ወደ 250,0000 ሰው ሞቷል::

እንዲሁ በዴርሡልጣን ምክንያት በአሁን ወቅት በመነኮሳት መሀል ያለው እስከ ደም መፋሰስ የደረሰው ግጭት ተባብሶና ከሌሎች የኢኮኖሚና የአካባቢው ፖለቲካ ችግሮች ተደምሮ፣ በኢትዮጵያና በግብፅ መሀል ግጭት ሲያስነሳ ይችላል:: ለምሳሌ:- የአባይን ወንዝ አጠቃቀም፥ ኤርትራንና ሶማሊያን በተመለከተ ኢትዮጵያና ግብፅ የሚከተሏቸው የየራሳቸው ፓሊሲዎች በሁለቱ ሀገሮች መሀል አለመግባባትን የፈጠሩበት ጊዜ ነበሩ::

አጠር ባለ መልኩ -የዴርሡልጣን ችግር ያለውን የጊዜ ርዝመትና ያለውን ውስብስብነት የተመለከተ ታዛቢ፣ መፍትሄ የሌለው ችግር አድርጎ ያስባል:: ነገር ግን ልብ ብሎ ለተመለከተው መፍትሄ መጥፋት ሳይሆን በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በተለይ በሕግና በዲፕሎማሲ ባለሙያዎችና በሚመለከታቸው የመንግስት ባለስልጣኖች መፍትሄ ለመፈለግ በቂ ጥረት እንዳልተደረገ፣ የተደረጉትም ጥረቶች በዘዴና በቀጣይነት እንዳልተደረጉ ይረዳል:: በዚህም የተነሳ ችግሩ እየከፋ ያለ ቢሆንም በአሁን ሰአት ለዴርሡልጣንን ችግር መፍትሄ ለማግኘት ጥሩ አጋጣሚዎች አሉ::



## ምዕራፍ ሶስት - ሃይማኖታዊ ትርጉማቸው፥ ታሪካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው

በቅድስት ሀገር ያሉት የኢትዮጵያ ቦታዎች ከፍተኛ ሃይማኖታዊ ትርጓሜ የሚሰጣቸው፥ የኢትዮጵያን ክርስትና ለሌላው ዓለም ለማስተዋወቅና ኢትዮጵያን ከውጪው አለም ጋር ለማገናኘት አገልግለዋል:: በተጨማሪ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አላቸው::

### ሃይማኖታዊ ትርጉማቸው

እነኚህ ቦታዎች ከጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክክርስቶስ ውልደት፥ ጥምቀትና ትንሳኤ እንዲሁም ክርስቶስ ተአምራት ከሰራባቸው ቦታዎች አጠገብ ስለተሰሩ ለክርስቲያኖች ከፍተኛ ትርጓሜ አላቸው::

የተወሰኑት ለመጥቀስ ያህል:- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የቅዱስ በአለወልድ (የመካነ ልደቱ ደብረ ሰላም ኢየሱስ) ቤተክርስቲያን ቤተልሔም ውስጥ፣ ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክክርስቶስ መወለዱን የምስራች የተነገረበት ቦታ አጠገብ ነው የተሰራው::

> *ሉቃስ ፪:፰-፲፬*
> *በዚያም ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ:: እነሆም የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ፣ ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ:: መልአኩም እንዲህ አላቸው:- እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና:: ይህም ምልክት ይሆንላችኋል ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግም ተኝቶ ታገኛላችሁ:: ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ:: እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ:- ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ስላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ::*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ክርስቶስ የተጠመቀበት ቦታና የሥላሴዎች አንድነት የታየበት ሥፍራ አጠገብ ነው የተሰራው::

*ማቴዎስ ፫:፲፮-፲፯*

> *ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእሩሱም ላይም ሲመጣ አየ እነሆም፣ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ:- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ::*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መድኃኔ ዓለምና የሚካኤል ቤተክርስቲያን ዶርሡልጣን ውስጥ በኢየሩሳሌም ክርስቶስ የተሰቀለበትና ሞትን አሸንፎ የተነሳበት ቦታ አጠገብ ነው የተሰሩት::

*ማርቆስ ፲፮:፫-፮*

> *እርስ በርሳቸውም:- ድንጋዩን ከመቃብር ደጃፍ ማን ያንከባልልልናል? ይባባሉ ነበር፣ ድንጋዩ እጅግ ትልቅ ነበርና አሻቅበውም አይተው ድንጋዩ ተንከባሎ እንደ ነበር ተመለከቱ:: ወደ መቃብሩም ገብተው ነጭ ልብስ የተጎናጸፈ ጎልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩና ደነገጡ:: እርሱ ግን:- አትደንግጡ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ፣ ተነሥቶአል በዚህ የለም እነሆ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ::*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ምስካበ ቅዱሳን ተክለሃይማኖት ገዳም፣ ቢታንያ ውስጥ ጌታችን መዳኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አልአዛርን ከሞት በማስነሳት ተአምር የሰራበት ቦታ አጠገብ ነው የተሰራው::







**የ1997 ዓ.ም. የጥምቀት በአል፤ ዮርዳኖስ ወንዝ ላይ::**





*ዮሐንስ ፲፩:፵፩-፵፬*

> *ኢየሱስ ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ:- አባት ሆይ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ:: ሁልጊዜም እንድት ሰማኝ እወቅሁ ነገር ግን አንተ እነደ ላክኸኝ እመሰግንሃሁ:: ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ ነገር ግን እንተ እነደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለ ቆሙት ሕዝብ ተናገርሁ አለ:: ይህንም ብሎ በታላቅ ድምፅ:- አልዓዛር፣ ሆይ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ:: የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመገነዝ እንደ ተጠመጠመ ነበር:: ኢየሱስም:- ፍቱትና ይሂድ ተዉት አላቸው::*

ታሪካዊ ጠቀሜታቸው

እነዚህን ቦታዎች ያሰሩትንና ያገለገሉትን የሀይማኖት አባቶች ነገሥታትና ግለሰቦች ታሪክ ከማስታወስ ሌላ፣ የኢትዮጵያን ታሪክ፥ ባሕልና የአስተዳደር ስርዐቶችን ለውጭው አለም በማስተዋወቅና ኢትዮጵያን ከሌላው አለም ጋር ለማገናኘት አገልግለዋል::

በተለያዩ ዘመናት መካለኛው ምስራቅ ላይ ከፍተኛ ተፅኖ የነበራቸው ሀገሮች በቅድስት ሀገር የኢትዮጵያን ያህል ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ቦታዎች ሳይኖራቸው የኢትዮጵያ የሆኑ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ቦታዎች በነዚህ ቦታዎች ላይ መኖር፣ ኢትዮጵያ እንደ አሁኑ በረሀብና በኋላ ቀርነት በሌላው አለም እንደምትታወቀው ሳይሆን በአንድ ወቅት ጠንካራ ሀገር መሆኗን፥ የኢትዮጵያን ታሪክ፥ ጂኦግራፊና ባሕል ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ወደ እስራኤል ለሚመጣው ሀገር ጎብኚ እያስተማሩ ነው::

ለምሳሌ:- አበሻ ስፈር ባለውና ከኪዳነምሕረት ቤተክርስቲያን ትንሽ እርምጃዎች ወረድ ብሎ በሚገኘው የንግሥት ዘውዲቱ መታሰቢያ ሕንፃ ዙሪያ በዓለም ካርታ ላይ ኢትዮጵያ የት እንዳለች የማያውቁ ከእስራኤልና ከዓለም ዙሪያ የሚጎርፉ ጎብኚዎች ተሰብስበው፣ በአስጎብኚ ድርጅት ወኪሎች ስለ ኢትዮጵያ ታሪክና ጂኦግራፊ ገለፃ ሲሰጣቸው አጠገባቸው ቆሞ ወይም ሲያልፍ ለሚያዳምጥ ኢትዮጵያዊ የክብር ስሜት ነው የሚሰማው::



ኢየሩሳሌም ውስጥ ካሉት የክርስቲያን ማሕበረሰብ ጥንታዊ ከሚባሉት አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ የመነኮሳት ማህበር:: ወደ ቅድስት አገር ለሚመጡት ተሳላሚዎች ኢትዮጵያን ከማስተዋወቁ ሌላ በተለያዩ ጊዜያት ኢትዮጵያን ከውጪው የክርስትና አለም ጋር በማገናኘት አገልግለዋል::

*The history of the Ethiopian presence in Jerusalem is also the history of the geographical, cultural and political knowledge regarding Ethiopia in medieval Europe . . . It was also in Jerusalem that the medieval European ideas regarding Ethiopia and its sovereign Prester John, considered a potential ally in Christendom's war against Islam, were at least partly formed on the basis of the observation of the European pilgrims in the holy Land. It was these ideas, both true and legendary, that stimulated the projects of the navigators of the great European discoveries towards the end of the fourteenth century, and as such, the Ethiopian presence in Palestine played an important role in the history of modern times.*[9]

ለምሳሌ:-በ1441 እ.አ.አ. ፍሎረንስ ላይ ተደርጎ በነበረው የክርስትና ጉባኤ ላይ አፄ ዘረዓ ያቆብ ኢትዮጵያ እንድትወከል በፈለጉ ጊዜ፣ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ ራይስ በነበሩበት በአባኒቆዲሞስ የሚመራ የኢየሩሳሌም የመነኮሳት ቡድን ነበር የላኩት::[9]

ከእስራ ሰባተኛው ከፍለ ዘመን መጨረሻ በኋላ ከኢትዮጵያ የሚላከው እርዳታ በተቋረጠበት ጊዜ አብዛኛዎቹ ወደ አውስትሪያ፥ እስፔን፥ ጣልያንና ወደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የተጠጉ ሲሆን፣ ከነኚህ መነኩሴዎች መሃል በኢትዮጵያ ቋንቋ፥ ታሪክና ባህል እንዲሁም ፍልስፍና በደንብ የተካኑ ምሁራን መነኩሴዎች ይገኙበት ነበር::

ለምሳሌ:- አውሮፓ ውስጥ የግዕዝን ፊደላትና ሰዋሰውን ያስተምሩ የነበሩት የዋልድባው አባ ቶማስ:: የተለያዩ የግዕዝ ፅሁፎችንና ፀሎቶችን ወደ ላቲንኛ የተረጎሙት፥ የግዕዝ ሰዋሰውን የፃፉትና

የሕንዱ ጴጥሮስ የሚል ስም የተሰጣቸው አባ ተስፋ ፅዮን ምሳሌዎች ናቸው::

አውሮፓውያን ከእነኚህ መነኩሴዎች በሰሙት የኢትዮጵያ ታሪክ ተደንቀዋል::

በዚህም የነተሳ አንደኛ:- በምስራቁ አለም የምትገኝ ከጥንት ጀምሮ ትፈለግ የነበረችው ንጉሷ ክርስቲያን ነው ተብሎ የሚታሰበው፣ ***የፕሪስተር ጆን*** ሀገር ኢትዮጵያ ናት ብለው አብዛኞቹ ማመን ይጀምራሉ::

ይሄ መተዋወቅ በኋላ ላይ በኦቶማን ቱርክ የተደገፈው የግራኝ አሕመድን ጅሐድ ለማገዝ ለመጣው የፖርቱጋል ጦር አንዱ ምክንያት ነው::

ሁለተኛ ደቡብ አውሮፓን አስግቶ ከነበረው የእስላሞች ጦር ጋር ምዕራባውያን ለሚያደርጉት ትግል፣ ኢትዮጵያን እንደ ጥብቅ ወዳጅ አድርገው መመልከት ይጀምራሉ::

በተጨማሪ እነኚህ ቦታዎች ለኢትዮጵያ ነፃነት ከፍተኛ ድርሻ አበርክተዋል:: መጋቢት 1936 እ.አ.አ. ማጨው ላይ ከተደረገው ጦርነት በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከአጃቢዎቻቸው ጋር በመሆን በጅቡቲ ወደብ አድርገው ሐይፋ ከምትባለው የእስራኤል የወደብ ከተማ ግንቦት 1936 እ.አ.አ. ከገቡ በኋላ:: ንጉሡ ወደ እንግሊዝ ሀገር ሲሄዱ ተከትለዋቸው መጥተው የነበሩት ማኒስትሮች ያረፉትና የኢትዮጵያን አርበኞችን ያበረታቱ የነበረው አበሻ ሰፈር በሚገኘው የንግሥት ዘውዲቱ መታሰቢያ ሕንፃ ውስጥ ሆነው ነበር::

<u>ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው</u>

የእነዚህ ቦታዎች ዋና አላማ ሃይማኖታዊ አገልግሎት ቢሆንም በአሁን ሰአት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ይደግፋሉ::

በባለሙያ ከተያዙ ደገሞ ለገዳማቱ ማህበር ተርፈው ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው የስብከተ ወንጌልና ሰብአዊ አገልግሎት በአሁኑ ሰአት ካለው በተሻለ ደረጃ ድጋፍ መስጠት ይችላሉ::



የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የሚደግፉት አንደኛ:- ለገዳማቱ መተዳደሪያ ከኢትዮጵያ መምጣት ያለበትን በማስቀረት ሲሆን

ሁለተኛ:- ከእነዚህ ሕንፃዎች የሚገኝ ግምቱ ከፍተኛ የሆን ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ስለሚላክ ነው::

አበሻ ሰፈር ላይ ካሉት በሀይማኖት አባቶች በነገሥታትና በግለሰቦች ከተሰሩት በርካታ የኪራይ ሕንፃዎች መሀል ይህን በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ ሊጠቀስ የሚቻለው የዘውዲቱ መታሰቢያ ሕንፃ ነው::

ይሄ ሕንፃ ሲሰው ያሀል የገዳማቱ ሲሆን የቀረው የኢትዮጵያ መንግስት ንብረት ነው::

ይሄ ሕንፃ 100 አካባቢ ክፍሎች ሲኖሩት የኢትዮጵያ ገዳማትና



የነቢያት መንገድ-38 የሚገኘው የንግሥት ዘውዲቱ መታሰቢያ ሕንፃ::

መንግስት ንብረት ጥበቃ ሀላፊ ቢሮና ማረፊያ ክፍሎች በስተቀር የተቀሩት በሙሉ ተከራይተዋል::

ዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ያለው የቅድስት ስላሴ ገዳም ውስጥ ቀድሞ እንደነበረው የልማት ተግባር፤ እንዲሁ በኢያሪኮ ገዳምም ያለ ሲሆን:: አሁን ያለው የልማት ስራ በባለሙያ ከተሰራና የገዳማቱ አስተዳደር የልማት ስራን ሀሳብ ተግባራዊ እንዲሆን መወሰን ከቻሉ:: አሁን ያለው የወይራ ፍሬ፥ የተምርና የብርቱካን ልማት ተስፋፍቶ ለገዳማቱ መተዳደሪያ የሚሆን ከፍተኛ ገቢ ሊያስገኝ ይችላል::

በቢታንያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ምስካበ ቅዱሳን ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን ገዳም ውስጥ ያለ- የአካባቢው ነዋሪዎች አገልግሎት አለመስጠቱን አይተው ለመውሰድ የሚፈልጉት ሰፊ ቦታ ላይ፣ በእስራኤል ያሉ ሎሎች አብያተ ክርስቲያኖች እንደሚያደርጉት የልማት ስራ መስራት ይቻላል::

በቤተልሔም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ በአለወልድ ቤተክርስቲያን አጠገብ ለእንግዳ ማረፊያ የሚሆን ባለ ሶስት ፎቅ ሕንፃ አለ:: ባለፉት ሶስት አመታት ተፋፍሞ በነበረው የፍልስጥኤሞችና እሥራኤሎች ግጭት፣ በተለይ የአጥፍቶ ጠፊ ቦንቦች ምክንያት አገር ጎብኚዎችና ተሳላሚዎች ቁጥር ቀንሶ ገቢ ማምጣት ባይችልም መረጋጋት ሲመለስ ለገዳማቱ መተዳደሪያ ገቢ ያመጣል::





የተምር፣ የወይራና የብርቱካን ልማት በኢያርኮ የቅድስት ሥላሴ ገዳም::

## ምዕራፍ አራት - እነዚህን ቦታዎች ለመስራት እና ለመጠበቅ የተደረጉ ጥረቶች

እነዚህን ቦታዎች ለመስራትና ለመጠበቅ በተለያዩ ወቅቶች የነበሩ አስተዳደሮች፥ የሀይማኖት አባቶችና ግለሰቦች ጥረቶች አደርገዋል::

### ኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩ አስተዳደሮች

በቅርብ ዘመናት እንደሚታየው ሳይሆን ቀድሞ የነበሩ የአክሱም፥ የዛግዌና ከዚያ በኋላም የነበሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት በቅድስት ሀገር የሚገኙትን የኢትዮጵያ ቦታዎች ለመጠበቅና ለማደራጀት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል::

ጎልጎታን ያሰራው የሮሙ ገዢና የንግሥት እሌኒ ልጅ የነበረው ኮንስታንቲን፥ ለአክሱም ነገስታት ለነበሩት ለኢዛናና ወዛይና (አብርሃ ወአጽብሐ) በወቅቱ የፃፈው ደብዳቤ:: በሁለቱ መሀል የነበረውን የሃይማኖትና የነበረውን የንግድ ጥሩ ግንኙነት የሚያሳይ ሲሆን ከላይ የተጠቀሰውን ፅሑፍ የሚደግፍ ነው:-

> *"Victor Constantius Maximus Augustus to Ezena and Shaizana. It is our greatest care and study as God knows – I think in fact in such things for all the human race – I to lead them to a knowledge of God, transforming life by hope, and in nothing dissenting in respect of the search for the just and true. …"* [10]

አፄ ካሌብ በአለም *ታሪክ* ላይ ወደ ደቡብ አረቢያ በ523 እ.አ.አ. (እስልምና አረቢያ ውስጥ ከመጀመሩ ከመቶ አመታት አካባቢ በፊት) ባደረጉት ዘመቻ ይታወቃሉ::

በአፄ ካሌብ ጊዜ የአክሱም ግዛት *ሂመያርና ሳባን* ጨምሮ ወደ ሰሜን አረቢያ ከፍ ብሎ እስከ *ናግራንና ዛፋር* ይደርስ ነበር::

በዚሁ ጊዜ *ናግራንና ዛፋር* ላይ የአክሱም ወታደሮች ምሽጎች ነበሩ:: በወቅቱ ደቡብ አረቢያ ውስጥ ጣኦት አምላኪ የነበሩትን የአካባቢ ነዋሪዎች ወደ ክርስትና በመቀየር፣ ደቡብ አረቢያ ውስጥ አክሱማውያን ክርስትናን አስፋፍተዋል::



እንዲሁም በቲቶ መሪነት ሮማውያን ኢየሩሳሌም የነበረውን ሁለተኛውን ቤተመቅደስ በ70 እ.ኤ.አ. ካፈረሱ በኋላ ወደ ደቡብ አረቢያ በርከት እያሉ ይፈልሱ የነበሩት አይሁዶች ምክንያት፣ የአካባቢው ነዎሪዎች እምነተ አይሁድን መከተል ጀምረው ነበር:: እምነተ አይሁድን ከተቀበሉት የአካባቢው ነዎሪዎች መሀል *ዱኑዋስ* ( በኋላ ላይ ዮሴፍ) የተባለ ባላባት ነበር::

ዱኑዋስ የአረቢያን ግዛት ለመቆጣጠር ባለው ፍላጎት የተነሳ በመጀመሪያ *ዛፍራን* ከዚያም *ናግራን* መሽገው የነበሩትን የአክሱም ወታደሮች ይፈጅና ሕዝቡን ከክርስትና ወደ አይሁድነት ተቀየሩ በማለት እምቢ ያሉትን ክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን ውስጥ ሰብስቦ በእሳት አቃጥሎ ፈጅቶ ነበር::

ይሄ ድርጊት በዓለም ላያ ያሉ ክርስቲያኖች ዘንደ ይለማና ለክርስቲያኖች በወቅቱ ሀዘንና ንዴት ፈጥሮ ነበር::

በወቅቱ በዓለም ላይ ከነበሩት ሀያላን ነገሥታት መሀል ለዚህ ድርጊት አፀፋ መስጠት የሚችሉት የቢዛንቲን ገዢ ቀዳማዊ ጀስቲንና የአክሱሙ ገዢ አፄ ካሌብ ነበሩ::

በዚህም የተነሳ *ቀዳማዊ ጀስቲን* እስክንድርያ ለነበሩት ለኮፕት ፓትርያርክ ለጢሞቲዎስ ሶስተኛ (518-535 እ.ኤ.አ.) አፄ ካሌብን እንዲገፋፏቸው መልክት ልኮ ነበር::

ፓትርያርክ ጢሞቲዎስ በበኩላቸው አስራ ሁለት መነኮሳትን መልከት አስይዘው ወደ አፄ ካሌብ ላኩ::

ለቀረው ዓለም ደቡብ አረቢያ የደረሰው ድርጊት እንደ ክርስቲያኖች እልቂት ሲታይ ለአክሱማውያን ግን እንደ ግዛት መነጠቅና እንደ ውርደት ጭምር ነበር የታየው:: በዚህም የተነሳ መልእክተኞቹ አክሱም ሲደርሱ አፄ ካሌብን ለዘመቻ ሲዘጋጁ ያገኟቸዋል::

አፄ ካሌብ 70 ትልልቅ መርከቦችና 100 ትትንሽ መርከቦች አሰርተውና ተጨማሪ ለመጓጓዣ የሚሆኑ መርከቦች ተከራይተው:: በድምሩ 230 መርከቦች ይዘው:: አክሱም ይገኝ በነበረው ቅዱስ ካቴድራል አስቀድሰው፣ ከበዓለ ጰራቅሊጦስ በኋላ ወደ ደቡብ አረቢያ ይዘምታሉ::[10]

*በመልዕክቱም መነኮሳቱ ወደ ቦታቸው እንዲመለሱና ብሎም እንዲጠብቃቸው ለመነው:: ከሌድ ቢዮም የአንበሳ ውድምን ገጸ በረከት ተቀብሎ፣ ልመናውን ሰምቶ፣ መነኮሳቱን ወደ ገዳማቸው መለሳቸው:: ከዚያም ዘመን ጀምሮ ዴርሱልጣን ለኢትዮጵያውያን ተመልሶ ተሰጠ ሁለት መቶ ዓመት ያህልም በዕረፍትና በደስታ ተቀመጡ::*

*ይህም ሊታወቅ የኢጣልያ ታሪክ ጻሐፊ "እናሊስ ገሊል" የሚባል በሁለተኛው መጽሐፍ እንዲህ ይላል በኢየሩሳሌም የነበሩ ክርስቲያኖች ሁሉ በእስላም ክፋት ብዙ መከራን ተቀበሉ:: በኢየሩሳሌም አንዳችም ክርስቲያኖች ሳይቀሩ ተባረሩ:: ሁሉም ወደ ክርስቲያን አገር ሸሹ: ወደ እስክንድርያ የገቡ አሉ:: እስከ አራት ዓመት ድረስ ክርስቲያን አልነበረም:: በመስከረም ወር የኢትዮጵያ ንጉሥ አንበሳ ውድም ወደ ምስር ገዢ ከሊድ ቢዮ ከብዙ ገጸ በረከት ጋር መላኩ ተጠቅሷል :: ከዚህም ጀምሮ እስከ ሁለት መቶ ዓመት ድረስ 'ዴርሱልጣን በኢትዮጵያውያን እጅ ነበረ' በማለት ያስረዳል::"* [8]

**<u>አፄ ነአኩቶ ለአብ</u>** - *"በአስራ አንድ መቶ ለባት ዓመተ ምህረት መንሱር ስመ መንግስቱ ሱልጣን ሳላህ ዲን የተባለ የእስላም ንጉሥ በግብጽና በኢየሩሳሌም ነገሠ:: እርሱም በነገሠ በሁለተኛው ዓመት የኢትዮጵያ ንጉሥ ነአኩቶ ለአብ ወደ ሡልጣን ሠላህ ዲን መልክተኞች ላከ:: ወደ ሸሪፎችም ሁሉ እንዲሁ እያለ ይልክ ነበር 'በኢየሩሳሌም ያለ ዴርሱልጣን የሚባለው ቦታ የኛ ነው:: ዴርሱልጣን ማለትም የንጉሥ ቦታ (ርስት) ማለት ነውና ስሙም ይታወቃል::' እያለ ምስክር ያሳይ ነበር::*

*ነገር ግን ሡልጣን ሰላህዲን የንጉሥ ነአኩቶ ለአብ ልመና ቸል አለ እንጂ እሺ አላለም:: የንጉሥ ነአኩቶ ለአብ ሡልጣን ሰላህዲን ልመናውን ቸል እንዳለበትና ልመናውንም እንዳልተቀበለው አይቶ ደግሞ ወደ ሮም ሊቀ ጳጳሳት ወደ ሦስተኛው እስክንድር እንዲህ ሲል ላከ 'ሡልጣን ሠላህ ዲን የእስላም ንጉሥ ለግብጻውያን አድልቶ ዴርሡልጣን የሚባለውን በኢየሩሳሌም ያለውን ቦታዬን ከመነኮሳቱ ቀምቶ ለግብፃውያን ሰጥቶብኛል:: አንተ አስመልስልኝ::' ብሎ የከበሩ ሰዎችን መልክተኞች*



*አድርጎ ላከ:: እነርሱም መልክታቸውን ለጳጳሱ ሰጡ:: ጳጳስ እስክንድርም መልዕክቱን ሰምቶ ከሐኪም ፊልጶስ ጋር የመልዕክቱን ምላሽ እንዲህ ሲል ላከለት::*

*'በኢየሩሳሌም ያለውን ዴርሡልጣን የተባለ የኢትዮ-ጵያውያን' ርስት አስመልስለት አለ:: ሁለተኛው በሮም ከተማ ከቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የሚገኘ ውን የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ገዳም ወደ ሮም ለሚመጡ ኢትዮጵያውያን ማረፊያ ብሎ ሰጠ::*

*ይህች ቦታም እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያውያን ካቶሊኮች ገዳም ናት:: ዛሬ ግን ግብፆች ዴርሡልጣን ሠላህዲን ለኛ ሰለሰጠን ነው እንጂ፣ የሐበሻ ንጉሥ ርስት ስለሆነ አይደለም እያሉ ያወራሉ::"* [8]

**<u>ዓፄ ዓምደ ጽዮን</u>** - *"ከአሥራ ሁለት መቶ ዘጠና ስድስት እስከ አሥራ ሶስት መቶ ሃያ ሰባት ዓመተ ምሕረት ድረስ ለሠላሳ አንድ ዓመት ያህል በንግሥናው ሲቆይ ዴር ሥልጣን ገዳምን እየጠበቀ መጻሕፍትንም እየላከ ማኅበሩን ያጽናናቸው ነበር::*

*ይህም ሊታወቅ ኢዮብ አዶልፍ የተባለውን የጀርመን ሰው በጻፈው ታሪክ እንዲህ ይላል::*

*"ዝንተ መጽሐፍ በጸዕኩ አነ ዓምደ ጽዮን ንጉሥ ወስመ መንግሥትየ ገብረ መስቀል ንጉሠ ኢትዮጵያ ለእግዝእትነ ማርያም ዘኢየሩሳሌም ከመ ታስተስሪ ሊተኀበ ፍቁር ወልዳ እመ ይመጽእ በስብሐቲሁ ከመ ይረሲ ማህደርየ ምስለ ቅዱሳኒሁ ወኀሩያኒሁ ለዓለም ዓለም::*

*ኦ አበውየ ወአኃውየ እለ አንበብክምዎ ለዛቲ መጽሐፍ ዝክሩኒ በጸሎትክሙ ከመይምሐረኒ ወይሣሃለኒ ወይስረይ ኃጢአትየ ወይዘክረኒ በመንግሥቱ ወከመ ይዝክረኒ ወይዝክርክሙ*
*እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት"*

*በማለት የጻፉ መሆኑን መረዳት ተችሏል::* [8]

**ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ**- "በሸዋ ከአሥራ ስምንት መቶ ሠላሳ ስምንት- ሠላሳ አራት ዓመተ ምሕረት ነገሠ በነበረበት ጊዜ:: በዘመኑ ማሰፊያ ገድለ ተክለ ሃይማኖትና ግንዘት እስጽፎ ኢየሩሳሌም በዴርሡልጣን ገዳም ለሚኖሩ ማኅበር ከብዙ ምጽዋት ጋር ላከላቸው::

ይህም ሊታወቅ ፕሮፌሰር ሊትማን ባሳተመው የዴርሱልጣን ታሪክ እንዲህ ተጻፈ::

'ገድለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዘመነ ሉቃስ በወርኃ የካቲት በዐሰተ ቀዳሚት በአሥራ ወስድስቱ ሌሊት በአሥራ ወክልዔቱ መዓልት በጊዜ ተሰዓቱ ሰዐት:

ዝመጽሐፍ ዘሣህለ ሥላሴ ንጉሠ ሸዋ መፍቀሬ ምጽዋት ወአቡሁ ወልደ ጊዮርጊስ ወስን ሰገድ ወእሙ ዘነበ ወርቅን በማለቱ ይታወቃል::' "[8]

**ንጉሥ ኃይለ መለኮት** - "በሸዋ ከ1838-1846 ነግሦ በነበረበት ጊዜ እንዲሁ ወንጌል፣ ግብረ ኅማማት፣ ሰንክሣርና ግንዘት አጽፎ ለዴርሡልጣን ሰጥቷል:: በዚህም ፕሮፌሰር ሊትማን ባሳተመው ታሪክ

"ዝንቱ መጽሐፍ ዘኃይለ መለኮት ንጉሠ ሸዋ ወአቡሁ ሣህለ ሥላሴ ወእሙ ወለተ ማርያም ዘአጥረዮ በንዋዩ፣ ዘሠረቆ ወዘፈሐቆ በሥልጣነ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ውጉዘ ለይኩን "

ዳግመኛም ከዚህ ቀጥሎ ኃይለ መለኮት ንጉሠ ሸዋ ዘወሀበ ለዴር ሥልጣን 5ቱ መጻሕፍት ማለት 4ቱ ወንጌል ግብረ ሕማማት ሰንክሣር ገድለ ተክለ ሃይማኖት ግንዘት ከመ ይኩኖ መርሐ ለመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ይሆነው ዘንድ ሰጠን ይላል::"[8]

**ራስ አሊ እና ደጃዝማች ውቤ**- "የበጌምድርና የጎጃም መስፍን የሆኑት ራስ አሊ እና የትግሬ መስፍን የሆኑት



ደጃች ውቤ በመካከላቱ ላይ በየጊዜው የሚደርሰውን ችግር ከመሠረቱ ለማጥፋት ወደ ኢየሩሳሌም ቢላላኩ፡ ግብጾች ግን መክፈቻውንና ርስቱን አንሰጥም አሉ.. ሆኖም ግን እንደጥገኞች እንቀበላቸዋለን በማለት እምቢ አሉ:: [8]

በዚህም የተነሳ ራስ አሊና ደጃች ውቤ የመገናኛ ዘዴ በሌለበት በዚያን ወቅት በቡዙ ድካም ወደ እንግሊዝ ንግሥት ይላላኩ ነበር::

በሰኔ ሃያ ዘጠኝ አሥራ ስምንት መቶ ሠላሳ ሁለት ዓመት ቀን የጻፉት ደብዳቤ እንዲህ ይላል:-

ከርእሰ መኳንንት ራስ አሊ የተላከ

በእካላት ሦስት በመለኮት አንድ ከሆነው የእምላክ ባሪያ፣ ይድረስ ከእንግሊዝ ንግሥት፣ እንዴት ነዎ? በሰማይ ከፍታ ከምድር በላይ በደኅና ይኑሩ ይህንንም ማለት የማያልቅ ምኞት ስለርስዎ ደኅንነት አለኝ ማለቴ ነው:: እኔ ከርስዎ ጋር በፍቅር ለመኖር በጣም እመኛለሁ:: ተስፋም አደርጋለሁ:: የኔን ፍቅር ለመረዳት ይቻልዎ ይሆን? ለመሆኑ እርስዎ በሕይወት እያሉ በኢየሩሳሌም ያለንን ርስታችንን ለሰምን እንቀማለን? እንዳናጣ የሚገባውን ሁሉ ያድርጉልን::

በኢየሩሳሌም ካለው ከኢትዮጵያ ርስት በከፊል ተወስዶብናል እጅግ በጣም አዝነናል:: ለው ርስቱ ሊያጣ የሞተ ያህል የሚያስቆጥረው ነውና:: የሚያደርጉትንም ውለታ ሕዝባችን በታሪክ ሊያነበው እንዲኖር ያድርጉልን:: በርስዎ ዘመን መንግሥት ኢትዮጵያውያን በኢየሩሳሌም ያለውን ርስታቸውን ተቀሙ ሊባል እንዳይኖር እንዲያደርጉልን እንለምንዎታለሁ::

ስለዚህ በኢየሩሳሌም የሚገኘው የመንግሥትዎ ተወካይ ሳሙኤል ሰባተኛ ለወገኖቼ እንደጠበቃቸው ይሆን ዘንድ የዚህ ሁሉ ኃላፊነት ሥራ በጅዎ ነው:: ደግሞም የሚፈልጉትን ያስታውቁኝ እልክልዎታለሁ:: "[8]

**አፄ ምኒልክ** - *"በነገሡ ጊዜ በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ዜጎቻቸው ማኅበረ መነኮሳት የዴርሡልጣን ገዳም መክፈቻ በኮፕቶች እጅ ተይዞ በውስጡ የሚኖሩትም ሁሉ በሩ*


ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘእምነገደ፡ ይሁዳ፡ ዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ሥዩመ፡
እግዚአብሔር፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ። ይድረስ፡ ከማ
ኅበረ፡ ኢትዮጵያ፡ እለ፡ ሀለው፡ በኢየሩሳሌም። እንዴት፡ ሰነ
በታችሁ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡ ደኅና፡ ነኝ። ተራርቃችሁ፡
፩ን፡ መሆናችሁን፡ እጅግ፡ መልካም፡ አደረጋችሁ። ፩ የሐበ
ሻ፡ ሰዎች፡ ተጣልታችሁ፡ ለየብቻችሁ፡ መሆናችሁ፡ እጅግ፡
የሚያሳዝን፡ ነገር፡ ሆኖ፡ ነበር። ፩ላይ፡ ሆናችሁ፡ ሌላ፡ የሚ
ጠጣባችሁን፡ ጠላት፡ መመለስ፡ ትችላችሁ። አሁንም፡ ጉዳይ፡ በ
ያገኛችሁም፡ ወደ፡ ሬስ፡ መኮንን፡ [illegible]
ችሁ፡ ጨርሱ። ከዚህ፡ የሚተርፍ፡ እንደሆነ፡ ወደ፡ እኔ፡ ላኩብ
ኝ። እግዚአብሔር፡ የማይለቅቀውን፡ የዘለዓለም፡ ፍቅር፡ ይስ
ጣችሁ። በነሐሴ፡ ፲፬፡ ቀን፡ ተጻፈ፡ በአዲስ፡ አበባ፡ ከተማ፡
[illegible] ዓመተ፡ ምሕረት።

*ተቆልፎባቸው መግቢያና መውጫ ማጣታቸውን፣ ቤተክርስቲያናቸውም ተዘግቶ የሃይማኖት*



*አገልግሎት እንዳይፈጽሙ መደረጉንና በኮፕቶችም ተንኮል የሚፈጸምባቸውን ስቃይና የሚሠራባቸውን ግፍ በሰሙ ጊዜ:: በ1905 ዓ.ም. ደጃዝማች መሸሻ ወርቁን ልከው ከቱርክ ሡልጣን ዓብደል ሃሚድ ጋር በመላላክ የዴር ሡልጣንን ገዳም ቁልፍን ለማስመለስ ብዙ ደክመዋል::"*

ደጃዝማች መሸሻ በርትተው ከዴርሡልጣን በምሥራቅ በኩል የኢትዮጵያ መነኮሳት በነፃ የሚጠቀሙበት አዲስ በር አስከፍተውላቸዋል::

*"በተጨማሪ ለገዳማቱ መርጃና መተዳደሪያ የሚሆን ሁለት መቶ ሺህ ማሪያ ትሬዛ ብር በገዳሙ ስም ባንክ አግብተው በወለዱ እንዲረዱበት አድርገዋል::*

*እንዲሁም በደብረ ገነት ገዳም አጠገብ አንድ ትልቅ በኪራይ የሚያገለግል ቤት አሰርተው ለመታሰቢያ ሰጥተዋል::"* [8]



የዳግማዊ አፄ ምኒልክ መታሰቢያ ሕንፃ፣ በኢየሩሳሌም ኢትዮጵያ መንገድ-8።

ቤተክርስትያንና ቤተ ማኅበሩን ባንድ ሕንፃ ኢያይዘው ታላቅ ገዳም አሠርተው ቤተ-ክርስትያኑን በቅዱስ ሥላሴ ሥም በ1925 ዓ.ም. ሰጥተዋል:: አሁን በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ካሉት የክርስቲያን ማኅበሮች ይህንን የሚያክል የለም::

ለዚሁ ገዳምና ቤተ ክርስቲያን ለህንጻው መጠበቂያ፥ በገዳሙ ውስጥ እያገለገሉ ለሚኖሩት ኢትዮ-ጵያውያን መነኮሳት መተዳደሪያ፥ ለመሥዋዕት፥ ለዕጣንና ለመብራት መረጃ እንዲሆን በአዲስ አበባ አራዳ ጊዮርጊስ አጥቢያ ውስጥ የ6 ቤተሰብ መኖሪያ ቤት ሦስት ፎቅ ቤትና ቦታ ለዮርዳኖስ ቅድስት ስላሴ ገዳም አድርገው ሰጥተዋል:: ገዳሙም ይህንኑ ተረክቦ ለንብረቱ ወኪል ጠባቂና ገንዘብ ሰብሳቢ ሠራተኛ በመመደብ እየተቆጣጠረ ይዞ ነበር::

ኋላ ግን በአብዮታዊው መንግስት አዋጅ ቦታና ቤት ሲወረስ የገዳሙም ንብረት አብሮ ተወረሰ:: በኋላ የቤቶች አበል እንዲሰጥ በመንግስት ስለ ተፈቀደ እስከ አሁን በየወሩ ለገዳሙ ስለሚላክ ገዳሙ ይረዳበታል::" [8]

## በህይማኖት አባቶች

በአሁኑ ዘመን በህይማኖት አባቶች ጥረት እየተደረገ እንዳለው ሁሉ:: በቀድሞው ዘመን በርካታ የህይማኖት አባቶች በቅድስት ሀገር የነበሩትን የኢትዮጵያ ቦታዎችን ለመጠበቅና ገዳማትን ለማስፋፋት ብዙ ጥረት አድርገዋል::

ከአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ያሉትና ታሪካቸው ተመዝግቦ ማግኘት የተቻለው ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል::

**መምህር ወልደ ሰማዕት** - "በሸዋ ክፍለ ሀገረ ቡልጋ ከሚባለው ወረዳ የተወለዱ መናኝ ኢትዮጵያዊ ታላቅ ባለውለታ መምሕር ናቸው:: ከአፄ ዮሐንስ ዘመን መንግሥት ቀደም ብለው በምንኩስና ሕግ



ተወስነው በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በኢትዮጵያ ገዳም ይኖሩ ነበር::

መምህር ወልደ ሰማዕት በዘመናዊም ሆነ በመንፈሳዊ ዕውቀት የተራቀቁ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የነቁ:: የዓረብኛው ቋንቋ/ናሕዊ/ የሚባለውን አገባብ በደንብ የሚያውቁ ሰው ስለነበሩ በቋንቋ ማኅበሩን አገልግለውታል::

አፄ ዮሐንስ እንደነገሱ በኢየሩሳሌም ገዳማት ማኅበር በገዳሙ ሥርዓት ተመርጠው አበምኔት ሆነው በማኅበሩ ምርጫ ተሾሙ::

አፄ ዮሐንስ እንደነገሡ በኢየሩሳሌም ገዳማት ማኅበር በገዳሙ ሥርአት ተመርጠው በኢየሩሳሌም



ለኢትዮጵያ ገዳም ማኀበር አበምኔት ሆነው በማኅበሩ ምርጫ ተሾሙ::

> *ወዲያው ከማኅበሩ የመታወቂያ ደብዳቤ በማጻፍ ወደ አፄ ዮሐንስ በመሄድ የአጻፉትን ደብዳቤ አስረክበው ኃላፊነታቸውን አሳውቀው የኢትዮጵያን ገዳም ማኅበር የኑሮ ችግር ያስረዱ ጀመር:: ከዚያም አፄ ዮሐንስ በሊጋስነት በርከት ያለ ገንዘብ ወደ ኢየሩሳሌም ገዳም ይልኩ ጀመር::* [8]

> *መምህር ወልደ ሰማዕት ደብረ ገነት ገዳምን፣ አሁን የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ መኖሪያና በቅድስት ሐገር የኢትዮጵያ ገዳማት ጽሕፈት ቤት የሆነውን ሕንፃ ገዝተው እና ለገዳማቱ በርካታ ስራዎች አበርክተዋል::"*

መምህር ወልደ ሰማዕት በመጨረሻ በኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው የደረሰባቸው ድርጊት የሚያሳዝን ሲሆን እራሱን የቻለ ሌላ ታሪክ ነው::

መምህር ወልደ ሰማዕት ለማስታወስ ደብረገነት ገዳም ኢየሩሳሌም ውስጥ ሀውልት ተሰርቶላቸዋል::

<u>አባ ፊሊጶስ</u>

በኢየሩሳሌም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ሲሆኑ ትራንስፓርት ባልተስፋፋበት ዘመን ከኢየሩሳሌም እስከ ዮርዳኖስ ዋና ከተማ አማን ድረስ እየተመላለሱ የዴርሡልጣንን ጉዳይ በብርታት የተከታተሉ:: እንዲሁም የዴርሡልጣንን ታሪክ ሠነድና እየሩሳሌምን እወቁ በሚሉ መፅሐፍት መልክ አዘጋጅተዋል::

> *"በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን በሞት ሲለዩ የሚቀበሩበት በጽርሐ ጽዮን ነበር:: ባለመብቶቹ ስለከለከሉና የመቃብር ቦታ ስለታጣ*

> *የሚገዛ ቦታ አስፈልገው በቤታንያ አሁን ገዳምና መካነ መቃብር የሆነውን ቦታ ገዝተው ዙሪያውን በግንብ አሳጥረው መታሰቢያነቱ ለቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥሌሴ እንዲሆን በማሰብ ቦታው የተገዛበትን ሂሳብ ተቀብለዋቸው በስማአቸው እንዲመዘገብ አድርገዋል:: "*



<u>በግለሰቦች</u>

<u>የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት</u> - ደብረ ገነት ገዳም ውስጥ ሕንፃ አሰርቶ ሰጥቷል::

<u>አፈ ንጉሥ ነሲቡና ወ/ሮ ደስታ</u> - *"በኢየሩሳሌም ቦታና ቤት ገዝተው ለገዳሙ ሰጥተዋል::*

*ባለቤታቸው ክብርት ወ/ሮ ደስታ ከባላቸው ሞት በኋላ በትርፉ ቦታ ላይ ትልቅ ቤት በተጨማሪ ሠርተው ሁሉንም ለገዳሙ ሰጥተዋል::"* [8]

<u>እማሆይ ወለተ ተክሌ</u> - *"የወ/ሮ ደስታ እህት የሆኑት በዚሁ በአፈ ንጉሥ ነሲቡ ባሠሩት ቤት ጎን ሁለት ክፍል ቤት አሠርተው ለገዳሙ ሰጥተዋል::"* [8]

<u>ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ</u> - *"አንድ የተሠራ ህንፃ ገዝተው ለገዳሙ ሰጥተዋል:: "* [8]



**ክብርት ወ/ሮ አማረች ዋለሉ** - *"በኋላ እማሆይ አማረች በኢያሪኮ ከተማ አንድ ሰፊ ርስት ከነቤቱ ገዝተው ሰጥተዋል::*



*በኢየሩሳሌም ሙስራራ ከሚባለው ቦታ ላይ የነበራቸውን ቤት ለገዳሙ አውርሰዋል::*

*በደብረ ገነት አቅራቢያ በገዳሙ ቦታ ላይ ለመኖሪያቸው ያሠሩትን ሕንፃ በሕይወታቸው መጨረሻ ላይ ለገዳሙ አውርሰዋል::"* [8]

**ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ** *"በ1895 ዓ.ም.* (1887 እ.ኤ.አ) *በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ተልከው ከቱርክ ባለ ሥልጣን አብደል ሐሚድ ጋር*

*በመነጋገር የዴርሡልጣንን ገዳም ቁልፍ ለማስመለስ ብዙ የደከሙ ባለውለታ ናቸው::"*

**ክቡር ራስ ወልዴ** - *"በኢየሩሳሌም ውስጥ አንድ ቦታ ገዝተውና ቤት አሰርተው ለገዳሙ ሰጥተዋል::"*

**ልዑል ራስ እምሩና ባለቤታቸው ልእልት ጽጌ** - *"በኢያሪኮ ከተማ ከገዳሙ ጋር ቤት አሰርተው ለገዳሙ ሰጥተዋል::"*

**ወ/ሮ አልታየ ወርቅ** *"የክቡር ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ባለቤት ኢየሩሳሌም በሚገኘው በደብረ ገነት ገዳም ውስጥ አንድ ፎቅ ሕንፃ አሰርተው ሰጥተዋል::"*



**ወ/ሮ በየነች ገብሬ** - *"በኢየሩሳሌም ውስጥ ቦታ ገዝተውና ቤት አሰርተው ለገዳሙ ሰጥተዋል::"*

**ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ**- *"በኢያሪኮ ከተማ በገዳሙ ቦታ ላይ ያሰሩትን ቤት ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ለገዳሙ መገልገያ ሰጥተዋል::"*

**አቶ ይልማ ወልደ ገብርኤል**- *"በደብረገነት ገዳም ውስጥ የእንግዳ መቀበያ የምትሆን አንድ አነስተኛ ሳሎን በማሰራት ለገዳሙ ሰጥተዋል::"*

በአሁን ሰአት ላለው የሕንፃዎች በቁልፍ የመያዝ ችግር ጥሩ ምሳሌ የሚሆን የአባ ዘካርያስ ፈረደ ስራ ነው::

**አባ ዘካርያስ ፈረደ** - *"በአፈ ንጉሥ ነሲቡ መታሰቢያ ህንፃ ውስጥ በቁልፍ ተሸጠው ከነበሩት መካከል የአንድ ሰው መኖሪያ ቤት ገንዘብ ከፍለው አስመልሰዋል:: በኢያሪኮ አንድ ቤት አሰርተዋል:: በቤተልሔም ገዳም ገዳሙ ካሠራው ህንፃ ውስጥ ለወላጆቻቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ለሦስት ክፍል ቤት መስሪያ ገንዘብ አበርክተዋል::"*

## ሳሙኤል ጎባት

ሳሙኤል ጎባት ስዊሳዊ የፕሮቴስታንት ቄስ ሲሆን፣ በ1826




Bet Nicolayson- ያፎ በር፣ ኢየሩሳሌም የሚገኝ፣ የሳሙኤል ጎባት መታሰቢያ ሕንፃና ፀሎት ቤት:: ሐምሌ 2004 እ.ኤ.አ.




እ.አ.አ. ኢትዮጵያ ይላካል:: ኢትዮጵያ ከመሄዱ በፊት ካይሮ ግብፅ ይሄድና አማርኛ ይማራል:: ከዚያም በ1827 እ.አ.አ. ኢየሩሳሌም ደብረ ሡልጣን ይሄድና አማርኛውን ያሻሽላል:: ኢትዮጵያ ሄዶ በ1846 እ.አ.አ. ዴርሡልጣን ሲመለስ::

ችግር ላይ የነበሩት የኢትዮጵያ መነኮሳት በእሱ መምጣት ተደስተውና ተስፋ በማድረግ የከተማው በር ድረስ ሄደው ተቀብለውት፥ እሱም በራሳቸው ቋንቋ ሰላምታ እንደሰጣቸውና የደረሰባቸውን ችግር ሁሉ እንዳስረዱት:: *አሌክስ ደቫይን* (*Alex Devine*) ጠቅሷል:: [11]

ኮፕቶች የዴርሡልጣንን በር በመዝጋት የኢትጵያ መነኮሳት የተቸገሩበት ወቅት ስለነበር:: ራሲ አሊና ደጃዝማች ውቤ ለኢትዮጵያ መነኮሳት ሀላፊነት እንዲወስድ ሳሙኤል ጎባትን ይጠይቁታል:: እሱም በእንግዳነቴ ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ለተቀበሉኝ፣ እንዳገራቸውና ሕዝባቸው ወዳጅ ደስ ይለኛል:: ነገር ግን በህጉ መሰረት በእንግሊዝ ንግሥት ካልታዘዝኩኝ ስልጣን ስለሌለኝ ምንም ማድረግ አልችልም ብሎ መልስ ይሰጣል::



በዚህም የተነሳ በ1852 እ.አ.አ. አመቱ ማለቂያ ላይ በወቅቱ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ በነበረችው ጎንደር ላይ በንጉሡ፡ በራሲ አሊ፥ በደጃዝማች ውቤና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ካህናት ስብሰባ ተደርጎ ለእንግሊዝ ንግሥት፣ ሳሙኤል ጎባት ጠባቂ እንዲሆን ደብዳቤ ተጽፎ ነበር:: [11]

በዚህም የተነሳ የብሪታንያ መንግስት በኢየሩሳሌም የብሪታንያ ቆንስል ጀምስ ፊን እንዲረዳቸው ያዛል::

በመጋቢት 1862 እ.ኤ.አ. ተጨማሪ ቁልፍ ኢትዮጵያኖች እጅ እንዳለ ኮፕቶች ሲረዱና የኮፕት መነኮሳት ቁልፉን ለመቀየር ሲያስቡ ጠብ ተነስቶ ነበር:: በዚህም ጊዜ የኢየሩሳሌም ፓሻ ጦር አምጥቶ ሲገላግላቸው፣ በወቅቱ የብሪታንያ ቆንስል ጀነራል ጀምስ ፊን ራሱ በመገኘት ለኢትዮጵያ መነኮሳት መብት ተከራክሯል::

በተጨማሪም ሳሙኤል ጎባት ለኢትዮጵያውያን በማስተርጎም፥ በማማከር፣ መፅሀፍት ቤቱና የኢትዮጵያ ይዞታዎች ምን እንደሚመስሉ ከመቃጠላቸው በፊት ተመልክቶ ስለ ነበር፣ የነበሩትን የኢትዮጵያ የታሪክ ማስረጃዎች ንብረቶችና ይዞታዎች በመመስከር ትልቅ ውለታ ውሏል::

## ምዕራፍ አምስት - የተወሰዱ ቦታዎችና ለመወሰድ ያበቁ ምክንያቶች

በአክሱም ዘመነ መንግስት የኢትዮጵያውያን ቤተክርስቲያኖች ደቡብ አረቢያ ነበሩ:: በአስራ ሁለተኛው ክፍል ዘመን ግብፅ ውስጥ *ዋዲ ናትራን* ውስጥ የኢትዮጵያውያን የቅዱስ ኤልያስ የኢትዮጵያውያን ገዳም ነበር:: [10] በ1189 እአ.አ. ቆጵሮስ ላይ ኢትዮጵያውያን ከኮፕቶች ጋር የቅዱስ እንጦንዮስ ቤተክርስቲያን አቋቁመው ነበር፤ በኋላ ለቀው የመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን አቋቁመው ነበር::[10] *W. Lithgow* የተባለው ጎብኚ፤ ሙሴ ፅላቱን የተቀበለበት የሲና ተራራ ላይ በ1582 እ.ኤ.አ. ሁለት መቶ የሚሆኑ ኢትዮጵያውን በገዳም ምንኩስና እንደ ነበሩ ጠቅሷል። [10] ኢትዮጵያኖች *ዴርከማር* የሚባል ገዳም በ1823 እ.ኤ.አ. ሊባኖስ ውስጥ ነበራቸው።[12]

ከእነዚህ ቦታዎች በተጨማሪ በቅድስት አገር የኢትዮጵያ የነበሩና የተወሰዱ ዋና ዋና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው:-

1. ጎልጎታ ቤተክርስቲያን ውስጥ፥ የክርስቶስ መቃብር ራስጌ፤ አሁን ኮፕቶች የያዙት የድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን::
2. ጎልጎታ ቤተክርስቲያን ውስጥ አሁን የአርመን ቤተክርስትያን የያዙት የንግስት እሌኒ ቤተክርስቲያን ተብሎ የሚጠራው ቤተክርስቲያን::
3. አሁን ኮፕቶች ያሉበትና የኮፕት ገዳም ተብሎ የሚጠራው ቀድሞ የኢትዮጵያ መነኮሳት ገዳም እንደነበረ አቡነ ፊልጶስ "ኢየሩሳሌምን እወቁ" በሚለው መፅሐፋቸው ውስጥ ይጠቅሳሉ::
4. የዴርሡልጣን ቅጥር ዋና በር ቁልፍ፡
5. ፅዮን ተራራ ላይ ያለው "የዳዊት ዋሻ" የሚባለው ቦታ::
6. የእርገት ቀን ደብረዘይት ላይ የነበራቸው የፀሎት መብት::



7. ጌተሰማኒ የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበረው የመፀለያ ቦታ
8. ቤተልሔም የልደቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበረው የመፀለያ ቦታ::

ምንድ ነው ኢትዮጵያ እነዚህን ቦታዎች እንድታጣ ያደረጋት?

ሰፊ ማብራሪያ የሚፈልግ ጥያቄ ሲሆን በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ባጭሩም ቢሆን ይመለሳል::

ስነዚህና ለሌቹም የኢትዮጵያ ቦታዎች መወሰድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዋና ዋና ምክንያቶች:- የቅድስት ሀገር በተደጋጋሚ መወረር፥ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት የነበረው የኦቶማን ቱርክ የመካከለኛው ምስራቅ በተለይ የኢየሩሳሌም አስተዳዳሪ መሆን፥ የኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግስት መዳከም፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሃላፊዎች የሆኑት ኮፕቶች በደል ዋናዎቹ ናቸው::

ኢየሩሳሌም በአብዛኛው የአለም ሕዝብ ህሊና ውስጥ ተቀርፃ ትኖራለች:: በዚህም የተነሳ በመካከለኛው ዘመን የተሰራ የዓለም ካርታ፤ ኢየሩሳሌምን የዓለም ማዕከል አድርጎ ነው የሚያሳየው::

በአለም ላይ የተነሳ ኃይለኛ አስተዳደር ሁሉ፤ በዓለም ሕዝብ ጭንቅላትና ልብ ውስጥ ያለችውን ኢየሩሳሌምን ሊቆጣጠር ያልሞከረ ትንሽ ነው::

ዋናዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል:- አሶሪያውያን፥ ባቢሎናውያን፥ ግሪኮች፥ ሮማውያን፥ ቢዛንቲኖች፥ ፋርሶች፥ እስላሞች፥ መስቀላውያን (ክሩሴደርስ)፥ ሞንጎላውያን፥ መምሉኮች፥ ቱርኮች፥ እንግሊዞች ናቸው::

ቅድስት ሀገርን የተቆጣጠሩ አስተዳደሮች ጎልጎታንና በዙሪያው ያሉትን ቅዱሳን ቦታዎችን ቀድሞ ይዟቸው የነበረውን የሃይማኖት ማህበር አስለቅቀው ለሌላው መስጠት በተደጋጋሚ ደርሷል::



ጎልጎታ መግቢያ ላይ ያለ፥ ክርስቶስ የተገነዘበት ቦታ::

ለምሳሌ:- መስቀላውያን (ክሩሴደሮችን) ኢየሩሳሌምን ያስተዳድር የነበረውን ፋጥማዊ የእስላሞች አስተዳደር አስወጥተው ኢየሩሳሌምን በ1099 እ.ኤ.አ. ሲይዙ፣ ጎልጎታ ውስጥ ቀድሞ የነበረው የቢዛንቲን ሊቀ ጳጳስ ፋንታ የላቲን (ካቶሊክ) ሊቀ ጳጳስ ነበር ያስቀመጡት:: ይህ የላቲን ሊቀ ጳጳስ የምስራቅ ቤተክርስቲያናት (ኦርየንታል ቤተክርስቲያናት) መነኮሳትን ከጎልጎታ ቤተክርስቲያን አስወጥቷል::

በሠላሀ ዲን መሪነት የእስላሞች ጦር በ1187 እ.ኤ.አ. ኢየሩሳሌምን ሲይዝ፣ በበኩሉ የላቲኖችን (ካቶሊኮችን) ሊቀ ጳጳስ አንስቶ የቢዛንታይን ሊቀ ጳጳስ ነው ያስቀመጡት::



ዴርሡልጣን የነበረው የኢትዮጵያውያን ቤት መፃሕፍት ስለተቃጠለ፣ በዚያን ወቅት ጎልጎታ ውስጥ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ላይ ምን እንደ ደረሰ ማስረጃ ማቅረብ ባይቻልም፣ ቅድስት ሀገር ላይ የደረሰው ተደጋጋሚ ወረራ እነደ ሌሎቹ የምስራቅ አብያተክርስቲያናት (ኦርየንታል አብያተክርስቲያናት) የኢትዮጵያ መነኮሳትም እንዳይደራጅ ማድረጉ አለቀረም::

እንዲሁም የኦቶማን ቱርክ ወደ መካከለኛው ምስራቅ መምጣት በተለይም ኢየሩሳሌምን መያዝ የተነሳ እና የኢትዮጵያ መእከላዊ መንግስት መዳከም፣ የኢትዮጵያ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ቦታዎች በሌሎች እንዲወሰዱ ምክንያት ሆነዋል::

ይሄ የሆነው ግን እንደዚህ በአጭር ዘመን ውስጥ አይደለም::

ኢየሩሳሌም ልክ እንደ አክሱም፣ የአክሱማውያንን አስተዳደር ትኩረት ይዛ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል::

> *While recent political event and decisions have placed Ethiopia firmly within her geographical setting, the continent of Africa, her traditional historical role – extending over two millennia or more – had made her a bridge between the civilizations of Africa and Asia. Many of her inhabitants were migrants from South Arabia who had introduced their language, their writing system, and other facets of their cultural inheritance. With her ancestry across two continents and her commanding position in the horn of Africa, Ethiopia has always occupied a favored place at a crossroads of civilizations and a meeting point of many races and influences. Jerusalem became as vital as Aksum in Ethiopian national consciousness, and Islam has exerted a more than intermittent pressure on the monophysite creed of Alexandria which is so deeply rooted in realm of the Prester John.* [13]

በዚህ ወቅት ከነበሩት ነገስታት መሀል ለምሳሌ:- በምስራቅ አፍሪካ ጠንካራ መሪ የነበረው አፄ ዓምደ ጽዮን (1313-1344 እ.አ.አ.)፥ እስከ ላኛው አባይ የግብፅ ግዛት እስከ *አስዋን* ድረስ በመሄድ

የግብፅ *መምሉኮች* ላይ ጥቃት ያደረሰው አፄ ዳዊት፥ አፄ ዘረዓ ያዕቆብና ሌሎችም ነገስታት፣ ከጥንት ጀምሮ እንደሚያደረገው በቅድስት ሀገር ያሉትን መነኮሳት ማህበር መጠበቃቸው ሲሆን::

> *"አነ: ዐምደ: ጽዮን: ንጉሥ: ወስመ: መንግሥትየ: ገብረ: መስቀል: ንጉሠ: ኢትዮጵያ: ለእግዝእትየ: ማርያም: በኢየሩሳሌም: ከመ: ታስተስሪ: ሊተ: ኀበ: ፍቁር: ወልዳ: ከመ: ይመጽእ: በስብሐቲሁ: ከመ: ይረሲ: ማኅደርየ: ምስለ: ቅዱሳኒሁ: ወኀሩያኒሁ: ለዓለመ: ዓለም: አሜን::"*[12]

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ቅድስት ሀገር ትተዳደር የነበረው፣ ኢትዮጵያውያን ነገስታት በኃይልና በተለይ አባይ ወንዝን በመጠቀም ጫና ያደርጉባቸው የነበሩት *መምሉክስ* በተባሉ ሱልጣኖች ስለነበር ነው::

*መምሉኮች* ከመካከለኛው እስያ በተለይ ከቱርክና ከጥቁር ባሕር አካባቢ በልጅነታቸው በባርነት ተገዝተው:: ከልጅነታቸው ጀምሮ ጥብቅ የውትድርና ስልጠና የተሰጣቸውና ግብፅን ሲያስተዳድሩ የነበሩት የአዩብ ሱልጣናዊ አስተዳደር ወታደሮች የነበሩ ሲሆኑ፣ በኋላ ላይ የሚያገለግሉት የአዩባዊ አስተዳደር ሲዳከም መፈንቅለ ሱልጣን በማድረግ ስልጣን የጨበጡ ሱልጣኖች ናቸው::

*መምሉኮች* በተዋጊነታቸው ሲታወቁ፣ በተለይ *ክሩሴደርስ* የተባሉ አውሮፓውያን የመስቀል ተዋጊዎችን አሸንፈው ቅድስት ሀገርን ይዘውና በወቅቱ መካከለኛው ምስራቅን የወረሩትን *ሞንጎልያውያንን* በጦር አሸንፈው ነበር::

እንዲሁም እስልምናንና የእስልምና የሕንፃ አሰራርን በኢየሩሳሌም አስፋፍተውና ጎልጎታ ቤተክርስቲያን ለመግባት ግብር ያስከፍሉ ነበር::



ለምሳሌ:- *በመምሉክ ሱልጣን ናዚር ቢን ቀላን* (1299-1309 እ.አ.አ.) ጊዜ የወጣ ትእዛዝ ይህንን የሚደግፍ ነው:: ክርስቲያኖችን መለየት እንዲቻል ሰማያዊ ኮፍያ እንዲለብሱ፣ መሳሪያ እንዳይዙ፥ የስቅለት በአል ባደባባይ እንዳያከብሩ፣ የቤተክርስቲያን ደውሎች እንዳይደወሉ የመሳሰሉ ትዛዛት አስተላልፎ ነበር::[9]

በተጨማሪም በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ፣ የአዳልና የይፋት ሱልጣኖችን በመርዳት ኢትዮጵያ ውስጥ እስልምናን ለማስፋፋት ማክረዋል::

በዚህ *በመምሉኮች* ጊዜ በ1290 ላይ ንጉሥ ይግባ ፅዮን (1285-94 እ.አ.አ.) ኢየሩሳሌም ለሚገኙት የኢትዮጵያ የመነኮሳት ማህበር-ደብዳቤ፥ ስጦታዎችና መቶ ሻማዎች ልኮ በወቅቱ ለነበረው *ለመምሉክ ሱልጣን* ኢትዮጵያውያን ቤተክርስቲያን ሲገቡ ከግብር ነፃ እንዲሆኑ መልክት ልኮ ነበር::

በዚሁ *በመምሉክስ* ጊዜ ኢትዮጵያውያን በ1335 እ.አ.አ. ቤተልሔም ያለው የልደቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ቦታ እንደነበራቸው ያቆብ የተባለ *የቬሮና* ተሳላሚ ጠቅሷል::

በተጨማሪም ኢየሩሳሌም በዚያ ጥብቅ *የመምሉኮች* እስላማዊ አስተዳደር ስር በነበረችበት ወቅት፣ ኢትዮጵያውያን ከግብር ነፃ መሆን ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት መስቀል ለብሰው መሄድ ይችሉ እንደ ነበር ገልጿል::[9]

*የመምሉክ ሱልጣን ጃክማክ* የግብፅ ክርስቲያኖችን ሲያጠቃ፣ በ1443 እ.አ.አ. ከዘረዓ ያዕቆብ (1434-68 እ.አ.አ.) የተላከ ቡድን *ለመምሉክ ሱልጣን ጃክማክ* ከሰጠው መልክት ውስጥ:-

> *ከ... ንጉሠ ነገሥት ዘረ ያቆብ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለ... ሡልጣን አልዘሂር ጃክማክ... ሀገራችሁን የሚያለማው አባይ ከኛ ሀገር እነደሚፈስና ልንገድበው እንደምንችል ልብ አትሉም? በእግዚአብሔር ማመናችንና ላገልጋዮቹ ስንል ካልሆነ በስተቀር ከመገደብ ምንም የሚያግደን ነገር የለም:: ምን ማድረግ እነዳለብክ ገልጸንልሃልና ምን ማድረግ እንዳለብህ ማወቅ አለብህ::*

የሚል ይገኝበታል::

በ1481 ኢትዮጵያውያኖች አዲስ አቡን ለመጠየቅ በሄዱበት ወቅት የሚከተሉት ጥያቄዎችን ጠይቀው ነበር፥

1. ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ጎልጎታ ሲገቡ ከግብር ነፃ እንዲሆኑ።

2. የኢትዮጵያ ልኡካኖች ኢየሩሳሌም በሚኖሩበት ጊዜ ጎልጎታ ከሌላው አለም ለመጡ ክርስቲያኖችም ክፍት እንዲሆን ።

3. በዚሁ ጊዜም የኢትዮጵያን ልኡካን ቡድን ክብር ምክንያት በማድረግ ከሌላው አለም የመጡ ክርስቲያኖች ከግብር ነፃ እንዲሆኑ።

በየጊዜው እንደሚደረገው በ1481 እ.አ.አ. የኢትዮጵያ ልኡካን ቡድን ወደ ኢየሩሳሌም ሲደርሱ ከዓለም ላይ የመጡ ክርስቲያኖች በሙሉ ግብር ሳይከፍሉ ጎልጎታ ቤተክርስቲያን ገብተው እንዲሳለሙ የሚል ትእዛዝ ይዘው መጥተው ነበር።

ነገር ግን በኢየሩሳሌም የሱልጣን ከታቢ ተወካይ ኢትዮጵያኖች ይዘው የመጡትን ትዛዝ እምቢ ይልና ኢትዮጵያውያኖች ብቻ እንዲገቡ ይስማማል። ልኡካኖቹም ከሱልጣኑ ጋር ያደረጉት ስምምነት መከበር አለበት ብለው እጥብቀው ይጠይቃሉ። *ሙዲር አልአዲን አልአለሚ* የተባለው ታሪክ ፀሀፊ እንደመዘገበው በመጨረሻ ከሌላው ዓለም የመጡ ክርስቲያኖችም አብረዋቸው ገብተዋል።[9]

ኢትዮጵያውያን በአስራምስተኛ ክፍለ ዘመን በኢየሩሳሌም ውስጥ በመስፋፋት ከ1460-1480 እ.አ.አ. ባለው ጊዜ፣ ተጨማሪ ሁለት ቦታዎች ኢየሩሳሌም ውስጥ ያገኛሉ፡- ጎልጎታ ውስጥ የፀሎት ቦታና ፅርሀ ፅዮን ላይ ነብዩ ዳዊት መዝሙር የደረሰበትን ዋሻ አግኝተው ነበር።



በዚህም የተነሳ በ1480 እ.አ.አ. ኢትዮጵያኖች የሚከተሉት ቦታዎች ኢየሩሳሌም ውስጥ ነበራቸው[9] ፡-

1. ጉልላቱ ያለበት ቦታ የነበረው የጸሎት ቤት - ጎልጎታ ውስጥ። (*The chapel in the rotunda of the basilica of the the Holy Sepulchre*)

2. የማርያም ፀሎት ቤት-ጎልጎታ ውስጥ። (*The Chaple of Mary of Golgotha*)

3. የጎልጎታ እምድ ስር የነበረው ፀሎት ቤት ጎልጎታ ውስጥ። (*The Chaple of the Improperium*)

4. ፅር ጽዮን ላይ የነበረው የዳዊት ዋሻ። (*The Grotto of David*)

በአስራስድስተኛው ክፍለ ዘመን ላይ ሁለት ተጨማሪ ቦታዎችን አግኝተው ነበር፡- የማርያም መቃብር የነበረበትን ጌተሰማኒ እና ዮርዳኖስ ወንዝ ላይ የነበረው ቤተክርስቲያን ላይ ከኮፕቶች ጋር በጋራ የመጠቀም መብት አግኝተው ነበር።

በ1512 እ.አ.አ. የአብረሐም መስዋእት ተብሎ የሚጠራውን ክርስቶስ የተሰዋበት ቦታ አጠገብ የነበረውን ፀሎት ቤት እግኝተው ነበር።

የኦቶማን ቱርክ ከመምጣቱ ከሶስት አመታት በፊት፣ በ1514 እ.አ.አ. ቅድስት ሀገርን የጎበኘው *ቬኒስያዊው ባርቦኒ ሞርሳኒ*።

1. ጉልላቱ ያለበት ቦታ ያለው ፀሎት ቤት - ጎልጎታ ውስጥ።

2. የማርያም ፀሎት ቤት -ጎልጎታ ውስጥ።

3. የጎልጎታ አምድ ስር የነበረው ፀሎት ቤት - ጎልጎታ ውስጥ።

4. *ፅርሀ ፅዮን ላይ የነበረው የዳዊት ዋሻ::*

5. ቤተልሔም ውስጥ ያለው የልደቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ የራሳቸው የፀሎት ቦታ እንደነበራቸው የጠቅሳል:: (*...their own altar in the Basilica of the Nativity*)

*የመምሉኮች አስተዳደር በኦቶማን ቱርኮች ከመተካቱ ከአመት በፊት የመጨረሻው የኢትዮጵያ ተሳላሚዎች ቡድን በ1516 ኢ.ኤ.አ. ከካይሮ እንደተነሳ አረባዊው ታሪክ ፀሃፊ ኢብን ኢያስ ጠቅሷል::*

*ነገር ግን የኢትዮጵያ ንጉሣዊ  አስተዳደር በተለያዩ ምክንያቶች መዳከም የተነሳ እርዳታው ሊቀጥል ስላልቻለ ለቦታዎቹ መወሰድ አንዱ ምክንያት ሆኗል::*

*የኢትዮጵያ ንጉሣዊ አስተዳደር በ1525 እ.ኤ.አ በተጀመረው የአሕመድ ግራኝ ወረራ በደረሰበት ጉዳት ላይ በ1550 እ.ኤ.እ የተጀመረው የኦሮሞ ፍልሰትና የአሕመድ ግራኝ ወረራን ሊያግዙ የመጡትን የፓርቱጋል ሀይሎች ተከትለው በ1554 እ.ኤ.አ. የመጡት የካቶሊክ ሚስዮኖች ሕዝቡንና ንጉሡን ወደ ካቶሊክ እምነት ሊቀይሩ ባደረጉት ጥረት በተነሳ የርስ በርስ ጦርነት ምክንያት፣ የኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግስት ተዳከሞ ይፈርስና በየክልሉ መሳፍንቶች ይነሱና የዘመነ መሳፍንት አስተዳደር ይጀመራል::*

*ዘመነ መሳፍንት አፄ ቴዎድሮስ ማእከላዊ መንግስትን እስከመለሰ እስከ 1855 እ.ኤ.አ ድረስ ቆይቷል::*

*The Trials of the Christian Kingdom and the Decline of Imperial Power*

*From the mid-fifteenth through the mid-seventeenth century, Christian Ethiopians were confronted by the aggressiveness of the Muslim states, the far-reaching migrations of the Oromo, and the efforts of the Portuguese--who had been*



*summoned to aid in the fight against the forces of Islam--to convert them from Monophysite Christianity to Roman Catholicism. The effects of the Muslim and Oromo activities and of the civil strife engendered by the Portuguese left the empire much weakened by the mid-seventeenth century. One result was the emergence of regional lords essentially independent of the throne, although in principle subject to it.* [3]

ሁኔታዎች ኢትዮጵያ ውስጥ እንደዚህ ሲሆኑ መካከለኛው ምስራቅን፣ ኢየሩሳሌምን ጨምሮ የሚቆጣጠረው የኦቶማን ቱርክ ነበር:: ይሄም ለኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ቦታዎች መወሰድ ሁለተኛው ምክንያት ሆኗል::

የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የሚባል ስም የወጣላቸው የኦቶማን ቱልጣናዊ አስተዳደር የተመሰረተው፣ *የኦጉዝ ቱርኮች ጎሳና የጋዚዎች የጦር መሪ በነበረው ኤርቱግሩል ከሀን ልጅ በኦስማን* (በምእራባውያን አጠራር ኦቶማን) በ1301 እ.ኤ.አ. አካባቢ ነው::

የኦቶማን ቱርክ ንጉሶች አንዱ በነበረው በቀዳማዊ ሳሊም (1512-20 እ.ኤ.አ.) ጊዜ ይሀ ግዛት ወደ ደቡብ ተስፋፍቶ፣ ሶርያን፣ ግብፅንና ፓለስታይንን (ኢየሩሳሌምን በ1517 እ.ኤ.አ.) ይዞ ነበር:: እንዲሁም የእስልምናን ቅዱሳን ቦታዎችን የሆኑትን መካንና መዲናን በጠባቂነት እውቅና አግኝቶ ነበር::

አውሮፓውያኖች ይፈሩት የነበረውና ድንቁ ሱሌይማን (*Suleiman the Magnificent*) የሚሉት የቀዳማዊ ሰሊም ልጅ ሱሌይማን (1520-66 እ.ኤ.አ.) *ቤልግሬድን* ይዞ በ1526 እ.ኤ.አ. ዳኑብ የተባለውን አውሮፓ ውስጥ ያለ ክልል አጠቃልሎ፣ ወደ ምዕራብ አውሮፓ ወደ ውስጥ በመግባት *የኦስትሪያን* ዋና ከተማ *ቪዬናን* ከበ መያዝ ባይሳከለትም እዚያው አካባቢ ቆይቷል::

በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ሰሜን አፍሪካ ውስጥ ሞሮኮን የኦቶማን ግዛት ውስጥ ጠቅልሎና አልጄሪያ፣ ቱኒዝና ትሪፖሊ ተወካዮቹን ስይሞ ነበር:: በ1534 እ.ኤ.አ. *ኩርዲስታንና ሞሶፖታሚያን* ይዞና የፋርስ ባሕረ ሰላጤ ደርሶ ነበር::

*በተጨማሪም ደግሞ የኮፕት ቤተ ክህነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበላይ አስተዳዳሪ እንደመሆኑ መጠን የቤተ ክህነቱን ሀብትና አልባሳት ጭምር እየተቆጣጠረ ያስተዳድር ነበር። ኢትዮጵያውያኖችም በሃይማኖትና በመንፈሳዊ ሥርዓት ተመሳሳይ መሆናቸውን በመመልከት በኮፕቶች ላይ ፍፁም የሆነ እምነት እንደነበራቸውና በዚህም እስኳን የገዳማቸውን መጠሪያ ስንኳ ሳይቀር "የኮፕት ክርስቲያን ማኅበር" እየተባለ እንዲጠራ አድርጎታል። ይሁን እንጂ የኮፕት ማኅበር ይህ የነበረውን*

*የሃይማኖት የበላይ ሥልጣን መክንያት በማድረግ የኢትዮጵያውያን ይዞታ የሆኑትን ቦታዎች ቀስ በቀስ ወደራሳቸው እንዲዛወሩ በማድረግና ርስቶቻችን ናቸው በማለት መብት እስከ መጠየቅ ደርሰዋል። በዚህ እስኳን ዋና ዋናዎቹን መካነ ቅዱሳት እንዲለቁ እያደረጉና በነዚህም በተለቀቁት ቦታዎችና ሥፍራዎች እነርሱ ራሳቸው እየገቡ እንዲቀመጡባቸው ለማድረግ ምንም ያህል ችግር ሊገጥማቸው አልቻልም ነበር።*

በዚህን ወቅት ከኮፕቶች ጋር ግጭት ሲኖር ፍርድ የሚሰጠው የኦቶማን ቱርክ አስተዳደር ሲሆን፤ አድልዎ የሚያደርጉት እንደጠላት ከሚቆጥሯት ከኢትዮጵያ ለመጡት መነኮሳት ሳይሆን በስራቸው ላስቸው ከግብፅ ለመጡት ኮፕቶች ነበር።

"የኮፕት ክርስቲያን ማኅበር" ገዳም የተባረሩት ኢትዮጵያውያን መነኩሴዎች፤ ጄሩሣልማን ውስጥ ጊዜያዊ መጠለያ ስርተው መኖር ቀጠሉ።

ጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ እየኖሩ የኑሮቸው ሁኔታ እየከፋ ሄዶ ይባስ ብሎ በ1838 እ.ኤ.አ. በሽታ ይነሳና በጄርሠልማን ቅጥር ውስጥ የነበሩት ሲያልቁ፤ የጄርሠልማን ቅፅር ቁልፍና ወደ ጄርሠልማን ቅፅር ማስገባት የሚያስችለው የቤተክርስቲያኑ በር ቁልፍ በኮፕቶች ይወሰዳሉ።

በዚሁ የግብፁ አሊ ፓሻ ኢየሩሳሌምን በሚያስተዳድርበት ወቅት፤ በሽታ ገብቷል በሚል ሰበብ በሽታው የነበረበትን የመነኮሳቱን ማደሪያ ፋንታ የኢትዮጵያውያን ታሪካዊ ማስረጃዎች የነበሩትን መፅሐፍትና የነገስታት ደብዳቤዎች፥ ኢትዮጵያ ችግር ላይ



ስተሆን ፀልዩልን ድል ሲያደርጉ እግዚአብሔርን አመስግኑልን እያሉ የላኳቸው ደብዳቤዎችና ባጭሩ የኢትዮጵያን ሐዘንና ደስታ ግልባጭ የያዘ መፅሃፍት ቤት ኮፕቶች እንዲቃጠሉት ሳሙኤል ጎባት ጠቅሷል።

> *According to Gobat, the Copts also asked the Turkish authorities for permission to burn the place, under the pretext of cleansing it of the deadly plague. Permission was granted,*
>
> *but rather than burning the living quarters of the Ethiopians, as expected, since the contamination of the plague would have been concentrated there, the Copts chose to burn the library and all the documents it housed proving Ethiopian rights to the site. <u>All the invaluable books, manuscripts, and documents went up in flames.</u>*[5]

ባስቁት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ፋንታ የመጡት ኢትዮጵያውያን፤ በቁልፎቹ መወሰድ ለመግባትና ለመውጣት ተቸግረው ነበር። ኢየሩሳሌምን ለሚያስተዳድረው የቱርክ ፓሻ ቢያመለክቱም ቁልፎቹን ሊያስመልሱ አልቻሉም።

በ1863እ.ኤ.አ ጄርሠልማን ውስጥ የነበሩትን የአብያተ ክርስትያናት ቁልፎች እጃቸው አስገብተው ነበር። ሆኖም የኦቶማን ቱርክ አስተዳደር ለኮፕቶች በማድላት ቁልፎቹን ለኮፕቶች እንዲመለሱ ያዝና ኢትዮጵያውያን ቁልፎቹን መመለስ እምቢ ሲሉ፤ በሮቹ ላይ አዲስ መቆለፊያ ይሰራና መክፈቻውን ለኮፕቶች ሰጥቶ ነበር።

የኦቶማን ቱርክ ኢየሩሳሲምን በያዘበት፤ የአሕመድ ግራኝ ወረራና የዘመነ መሳፍንት ወቅት። እንዲሁም መነኮሳቱን የሚረዱ ጠንካራ ነገሥታት ባልነበሩበት ጊዜ ከጄርሠልማን በስተቀር ቀድሞ በቅድስት ሀገር የነበሩ ቦታዎች በሙሉ ተወሰዱ።

*When the last Ethiopian succumbed to the plague, the Coptic priest took the keys to the Ethiopian monastery and the chapel attached to it, under the influence of the Armenian Patriarch who wished to take possession of the chapel.* [5]

ከዴርሡልጣን ቅፅር ለመውጣትና ለመግባት የሚያስችለው የቤተክርስቲያኑ በር ቁልፍ ለኢትዮጵያውያን በአዲሲቱ እስራኤል መንግስት እርዳታ በ1970 እ.ኤ.አ. ሲመለስ፤ የዴርሡልጣን ቅፅር ዋና በር ቁልፍ አሁንም በኮፕት መነኮሳት እጅ ነው ያለው:: አሁን የቁልፉ በኮፕት እጅ መሆን የባለቤትነት አንዱ ማስረጃቸው ሆኖ መከራከሪያ ሆኖአቸዋል::

ባጭሩ ጥንት የነበሩ የኢትዮጵያ ቅርሶች- የቅድስት ሀገር ተደጋግሞ መወረር፥ መነኮሳቱን ይረዳና ይጠብቅ የነበረው ቀድሞ የነበረው ጠንካራ የኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግስት መዳከም፥ የኦቶማን ቱርክ መካከለኛው ምስራቅን መያዝና የኮፕት መነኮሳት የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት አስተዳዳሪ መሆን ተደምረው የኢትዮጵያ ሃይማናታዊና ታሪካዊ ቦታዎች ተወስደዋል::

በአሁን ጊዜ እንኳን የውጪ ሰውና ኢትዮጵያዊ ራስ ድሮ ጎልጎታ ውስጥ የክርስቶስን መቃብር አጠገብ ሆነው ቅዳሴ የሚያደርጉ የነበሩት ኢትዮጵያውያኖች ነበሩ፤ ኢትዮጵያኖች ጌተሰማኒ ውስጥና ቤተልሔም የልደቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ መጸለያ ቦታዎች ነበራቸው ቢሉት ለማመን ይቸግረዋል::



## ምዕራፍ ስድስት- አሁንም የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ስጋት

ከአስራ ስባተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እስከ አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በቅድስት ሀገር በሚገኙት የኢትዮጵያ ገዳማት የደረሰውን ችግር በመመልከትና በዚያም ምክንያት በተወሰዱት ቦታዎች በመቆጨት ከኢትዮጵያ እርዳታ እስከሚመጣ ከሚጠብቁ እዚያው ቅድስት ሀገር ውስጥ ቋሚ የሆኑ መተዳደሪያ ንብረቶች እንዲኖራቸው በማለት፤ አርቆ አስተዋይና ሰወገን ደንታ የነበራቸው ነገስታት፥ ግለሰቦችና የሀይማኖት አባቶች የተሰሩ ከኢየሩሳሌም እስከ ኢያሪኮ ያሉ ቦታዎች የቀድሞዎቹ ከጠፉባቸው የተሰዩ ምክንያቶች ቢሆንም እንደቀድሞዎቹ ሲጠፉ ነው::

ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ሲኖሩ ዋናዎቹ:-አንደኛ የመካከለኛው ምስራቅ ግጭቶች ሲሆን

ሁለተኛ ከኢትዮጵያውያኖች ጋር የተያያዘ ነው:: ያም ለነዚህ ቦታዎችና ሕንፃዎች ተገቢውን የኪራይ ውል አለማድረግና ውል ከተደረገም በኋላም ክትትል አለማድረግ

ሶስተኛው ምክንያት አሁንም ከኢትዮጵያውያኖች ጋር የተያያዘ ሲሆን፤ ያም እድሜያቸው በመግፋት ላይ ላሉት ሕንፃዎች ተገቢ እድሳት አለማድረግ ነው::

በአሁን ሰአት ትልቁ ችግር እነዚህ የገዳማቱ ማህበር መተዳደሪያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅርስ የሆኑ ንብረቶች በባለሙያዎች አለመጠበቃቸው ነው::

መፍትሄውም የገዳማቱ አስተዳደር ከሚያደርጉት ክትትል በተጨማሪ በመንበረ ፓትርያርኩና ሲኖዶስ፥ መንግስትና ምእመናኑ እራሱ፤ በተለይ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እነኚህን ቦታዎች መከታተል ነው::

የነዚህም ንብረቶች መጥፋት ውጤት:- ከእነሱ ጋር የተያያዘውን ሃይማኖታዊ ስራ፥ ታሪክና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ይዞት ይጠፋል::

ዮርዳኖስ ወንዝ ዳር የነበረው የሥላሴ ገዳምና ኢየሩሳሌም ውስጥ ሙስራራ ሰፈር የነበረውና ወይዘሮ አማረች ዋለሉ ለገዳማቱ

አባ አብረሐም ባይሩ እንደነገሩን፣ በቁልፍ ተይዞ ሙሉ በሙሉ የተወሰደ ሕንፃዎች ምሳሌ:-*ከስምንተኛው ምዕራፍ እና በገዳማቱ ጽሕፈት ቤት ሕንፃ መሀል ያለው ሕንፃ ሲሆን:: ሕንፃው በቁልፍ ከተያዘ በኋላ፣ በቁልፍ የያዘው ግለሰብ ሲታሰር ለእስልምና ሃይማኖት ንብረት ጠባቂ ድርጅት (Wakf) የሰጠው ሕንፃ ነው::*

ከኢየሩሳሌም ውጪም ኢያሪኮ ውስጥ ያፌ መንገድ-4/37 ላይ ያለ፣ ገዳሙ አከራይቶት በቁልፍ የተያዙ ክፍሎች ያሉት ሕንፃ አለ::

እዚህ ላይ ቤት ለማለት የተፈለገው፣ በአማካይ ሁለት መኝታ ቤትና አንድ ሳሎን እንዲሁም መታጠቢያና ማብሰያ ክፍሎች ያለው ቤት ወይም አፓርትመንት ተብሎ የሚጠራው ነው:: በዚያ ላይ በድሮ ጊዜ የተሰሩ አፓርትመንቶች ስለሆኑ አብዛኞቹ ትትልቅ ክፍሎችና መተላለፊያ ክፍል (ኮሪደር) አላቸው::

በዚህ መልክ የተያዙ አፓርትመንቶች ድምራቸው 15 አካባቢ ሲሆን፣ ወደ 45 ክፍሎች በቁልፍ ተይዘዋል ማለት ነው::

እንዲሁም የአፄ ኃይለ ሥላሴ/የእቴጌ መነን መታሰቢያ ሕንፃ-ሙሉውን በቁልፍ የተያዘ ሲሆን፣ ይሄንኑ በቁልፍ የተያዘ ቤትና አጠገቡ ያለ ቦታ የአፄ ኃይለ ሥላሴ የልጅ ልጆች ጠበቃ እና ***በእስራኤል የኢትዮጵያ ገዳማትና የመንግስት ንብረት ጉዳይ ፈጻሚ ጽሕፈት ቤት*** እስከ ዛሬ ድረስ ክርክር ላይ ናቸው::

የቁልፍ ደንብ የሚሰራው እስራኤል ውስጥ ላሉ ለሌሎች ሀገሮች ሕንፃዎችም ሲሆንና ሌሎች ሀገሮች የኪራይ ውልና ክትትል በማድረግ እዚህ ደረጃ እንዳይደረስ ሲያደርጉ፣ በዚህ ሕግ በተለይ የተጎዱት የኢትዮጵያ ሕንፃዎች ናቸው::

በዚህ ሁኔታ የሚኖሩ ሰዎች አሁን በብዛት ሲኖሩ የኖሩበትም አመታት መሸጥ የሚችሉበት ጊዜ ላይ ነው ያሉት:: ለምሳሌ:- የአፄ ምኒልክ መታሰቢያ ሕንፃ ውስጥ በቁልፍ መብት 33 አመት በላይ የቆየች ግለሰብ አለች:: የባልቻ አባ ነፍሶ መታሰቢያ ሕንፃ






**ኢየሩሳሌም ደቦራ ነብይት መንገድ-6**
**የአፄ ኃይለ ሥላሴ/እቴጌ መነን መታሰቢያ ሕንፃና ቦታ**

ውስጥ በቁልፍ መብት 42 አመታት በላይ የቆየች ግለሰብ አለች:: ሁለቱም ሲለቁ ቁልፉን ለሌላ ግለሰብ ወይም ለራሱ ለኢትዮጵያ ገዳም በበርካታ ገንዘብ ሸጠው መውጣት ይችላሉ::

ሶስተኛው የሚገርመውና የሚያሳዝነው ምክንያት፣ የቀድሞ ትውልድ በስንት ድካም ላሰራቸው ሕንፃዎች ተገቢውን እደሳት አለማድረግ ነው::

ይሄ የሚመለከተው መንበረ ፓትርያሩኩንና ሲኖዶሱን፣ በተለያዩ ዘመናት ለእነኚ ሕንፃዎች ሀላፊ የነበሩትን የገዳማቱን መጋቢዎችና በኢትዮጵያ ውጪ ጉዳይ ሚንቴስር ስር ***በእስራኤል የኢትዮጵያ ገዳማትና የመንግስት ንብረት ጉዳይ ፈጻሚ ጽሕፈት***

***ቤት ሀላፊ*** የነበሩትን ብቻ ሳይሆን፤ ብዙ ማድረግ ሲችል ምንም ያላደረገውን ምእመን በተለይ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ጨምሮ ነው::



**የአፈንጉሥ ነሲቡና ባለቤታቸው መታሰቢያ ፎቅ መግቢያ::**
**ስላንት-11 ኢየሩሳሌም**



የሌሎች ሀገሮች ሕንፃዎች የፅዳት ሠራተኛ፣ የጥገና ባለሙያና አትክልተኛ ተመድቦላቸው ጥበቃ ሲደረግላቸው፣ አበሻ ሠፈር ያሉት በርካታ የኢትዮጵያ ገዳማት ሕንፃዎች አንድም መደበኛ



**ኢየሩሳሌም ስላንት-2 መንገድ ውስጥ ያለ**
**የመምህር ወልደ ሰማዕት መታሰቢያ ሕንፃ**

የፅዳት ሠራተኛ፥ መደበኛ የጥገና ባለሙያና መደበኛ አትክልተኛ ሰራተኛ የላቸውም::

በዚህም የተነሳ ከውጪና ከውስጥ ወላልቀው፥ ተክሎች በቅለውባቸው፥ ግርጊዳዎቻቸውና መስኮቶቻቸው ተሰንጥቀው::

ከአካባቢው ካሉት የሌሎች ሀገሮች ሕንፃዎች ጋር ሲወዳደሩ ስፈሩን አሳጥተውት፣ ተከራዮች ጥገናዎች ካልተደረጉ ኪራይ አንከፍልም በማለት ኪራይ የሚከለክሉበት ጊዜ አለ::

በአሁኑ ሁኔታ ከተቀጠለ ኪራይ አንከፍልም ሳይሆን የሚከራያቸው አይኖርም::

በይበልጥ- አለመታደሳቸው እነዚህ ቅርሶች እንዲወሰዱ ምክንያት ፈጥሯል:: ለዚህም ምሳሌ የሚሆነው በአንድ አጥር ውስጥ ያሉት የአፈንጉሥ ነሲቡ ሕንፃ፥ የአፈንጉሥ ነሲቡ ባለቤት ወ/ሮ ደስታ መታሰቢያ ሕንፃና የባለቤታቸው እህት እማሆይ ወለተ ተክለ ሃይማኖት ሕንፃ ናቸው::




ስላንት-11 ኢየሩሳሌም

ከእነኚሁ ከገዳማቱ ሕንፃዎች ጋር ተያይዞ ያለ፥ ጥገና የሚፈልግና ባዶውን የነበረ ምድርና ፎቅ ቤት አጠገብ ያለ ቦታን ትልቅ የመኖሪያ ሕንፃ ሊገነባ ለሚፈልግ ድርጅት የኢየሩሳሌም ማዘጋጃ ቤት ሊሰጠው አስቦ፣ ፎቁና ምድር ቤቱ የኢትዮጵያ ገዳማት



ንብረት እንደሆኑ የኢየሩሳሌም ማዘጋጃ ቤት የኢትዮጵያ ገዳማት አስተዳዳሪዎችን ይጠይቃቸዎል::

የገዳማቱ አስተዳደር ምድር ቤትና ፎቁ የገዳማቱ ንብረት እንደሆነ ሲገልፁ፣ ማዘጋጃ ቤቱ የቤቱን ፕላን እንዲያሳዩ ጠይቀው የገዳማቱ አስተዳደር የምድር ቤትና ፎቁን ንድፍ ሲያጡ በማዘጋጃ ቤቱ ፈቃድ- ሕንፃ የሚሰራው ድርጅት ፎቅና ምድር ቤቶቹን ያፈርስና ከእነዚህ ሕንፃዎች ጋር አያያይዞ ትልቅ ሕንፃ እየሰራ ነው::

የምድር ቤትና ፎቁን አፍርሶ ቦታውን መውሰደው አልበቃ ብሎ:: በመጠኑ ትልቅ የሆነው ሕንፃ- ከገዳማቱ ሕንፃ ጋር ተያይዞ፥ የዘመናዊ የሕንፃ አሰራርን ደንብ በሚጋፋ መልኩ፥ የአየር መዘዋወር በሚከለክል መልኩ፥ ፀሀይ በሚከለክል መልኩና ወደ ፊት የቀሩትን ሕንፃዎች አፍርሶ ቦታውን ሊያጠቃልል በሚችል መልኩ ነው እየሰራ ያለው::

ይሄ የሚያሳየው ሌሎቹም ሕንፃዎች ካልተጠገኑ:: ለመኖሪያ ተጣቦ ያለው የአካባቢው ነዎሪ እስከሚፈርሱ እንኳን እንደማይታገሳቸው ነው::

አሁን ባለው ሁኔታ ከተቀጠለ ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ምክንያቶች በአጭር ዘመናት ውስጥ ሁሉም ሕንፃዎች ስለሚጠፉ በቅርብ ዘመናት ባለው ደካማ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ፣ እርዳታ ከኢትዮጵያ መጥቶና ቦታ አግኝቶ ሌሎች ሕንፃዎች በምትካቸው መስራት የሚቻልና ብሎም የገዳማቱን ማህበር ማስተዳደር የሚቻል አይደለም::

ስለዚህ ቀድሞ ከጎለጎታና ከሌሎችም ቅዱሳን ቦታዎች መውጣትና መነጠቅ እንዲሁም ለዴርሡልጣን ገዳም ችግር ምክንያቶች አንዱ ከሆነው የገንዘብ ችግር ውስጥ ዞሮ ዞሮ መመለስ ነው::

እነኚህ ብዙ ታሪክ ያላቸው፥ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው የስብከተ ወንጌል፥ ሰብአዊ አገልግሎትና ለኢኮኖሚ ድጋፍ የሚውሉና ጥንት ኢትዮጵያውያን እስከ ኢየሩሳሌም በእግር ተመላልሰው፥ ብዙ ድካም፥ ዝርፊያ፥ ሞት አጋጥሟቸውና ብዙ ገንዘብ የፈሰሰባቸው ሕንፃዎች ሊጠፉ ይችላሉ::

የሚያስፈልገው ሰፈር ሲኖር፤ በሌላኛው በኩል ቤን ይሁዳ ተብሎ የሚጠራው እየተስፋፋ ያለ የከተማው ዋና መናህሪያ መንገድ አለ:: አበሻ ሰፈር ያሉት ሕንፃዎቸ አሁን በሚታየው



**የደጃ/ች ባልቻ አባ ነፍሶ መታሰቢያ ሕንፃ መግቢያ ዶቦራ ነብይት-9 ኢየሩሳሌም**

ሁኔታ ችላ ቢባሉ ወደ *ሚአ ሸአሪም* ወይ ወደ *ቤንይሁዳ* መጠቃለላቸው አይቀርም::

**በቅርቡ ግልፅ ባልሆነ መልኩ በአካባቢው ነዎሪዎች የተያዘው የአፄ ኃይለ ሥላሴ ልጆችና መንግስት እየተከራከሩበት ያለው ኢየሩሳሌም ዶቦራ ነብይት-6 ላይ ያለ ቦታ ይሄንኑ የሚያጠናክር ነው::**



ሁለተኛ ምክንያት:- የራሳቸውን የጥገና ወጪ መሸፈን መቻላቸው ነው::

ለምሳሌ:- ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ አስገዝተውት ለገዳማቱ ማህበር ሰጥተውት አሁን ተጎሳቅሎ የሚታየውና *በሚአ ሸአሪም*ና በአበሻ ሰፈር ድንበር ላይ የሚገኘውን ብንወስድ፤ እዚያ ሕንፃ ላይ የሚኖሩት ተከራዮች የሚከፍሉትን ኪራይ ደምረን በአመት ወደ ሁለት መቶ ሺ ሼኬል አካባቢ ነው:: ለጥገናም የሚያስወጣው ወጪ ይህንኑ ያክላል:: ማለት:-ከሕንፃው የሚገኘው የአንድ አመት ገቢ ሊያሳድሰው ይችላል::

በዚሁ አይነት የቀሩትም ከሞላ ጎደል ከራሳቸው የሚገኘው ገቢ ራሳቸውን ማሳደስ ስለሚችል፤ በአመት አንዱ ሕንፃ እንኳን እራሱን እንዲያሳድስና ከቀሩት የሚገኘው ገቢ ለገዳማቱ መተዳደሪያ እንዲሆን ማድረግ የሚቻል ነው::

የገዳማቱ ማህበር ችግር የሚታይበት በንብረት አያያዝ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ክፍሎች ነው:: በገንዘብ አያያዝ፥ በጤናና ንፅህና አጠባበቅ:: እንዲሁም የስራ ቅደም ተከተል (ለምሳሌ:- ያሉት እየፈረሱ እያሉ ሌሎች ግንባታዎችን መጀመር)ና ዘመናዊ አሰራር ደረጃ ላያ ካለችው ከእሥራኤል ጋር የሚሄድ የስራ ቅልጥፍና አለመኖር ጭምርም ነው::

ኢትዮጵያን ሪፓርተር የተባለው መፅሔት በ12/10/2002 እ.አ.አ. በኢንተርኔት ላይ ያወጣው ፅሁፍ ይሄንኑ ይደግፋል:: በዚሁ መፅሄት መሰረት የገዳማቱ አስተዳደር ሶስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደጠፋበትና ምክንያቱም የገዳሙ አስተዳደር ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝን የማይከተል እንደሆነ ጠቅሷል::

ቀድሞ የነበሩ ተከራዮች ትተዋቸው የሚሄዱት የውሐ፥ የመብራት፥ የግብር(*አርኖና*) ውዝፍ በወቅቱ ተከታትሎ አለማስከፈል በእነዚህ መስሪያ ቤቶች እየተወቀሰ ያለው ገዳሙ ሲሆን፤ አዲስ ተከራዮች ከውሐ፥ ከመብራት፥ ከግብር (አርኖና) መስሪያቤቶች ጋር የሚያደርጉት ጭቅጭቅ ቀላል አይደለም::

በጤናም በኩልም- አገሪቱ ውስጥ በጣም የተለመደውን የህክምና ኢንሹራንስ እስከ ቅርብ ጊዜ ባለመገልገል ወይም እስራኤል ውስጥ ያሉትን ኢትዮጵያውያን የህክምና ባለሙያዎች

ባለመጠቀም የተነሳ መነኮሳቶች ለህመም ተዳርገዋል:: ለምሳሌ ጴሩሣሌም በር ላይ ይቀመጡ የነበሩ መነኩሴ፣ የነበራቸው ህመም ክትትል ማጣት የተነሳ ህመማቸው ተባብሶ አስቸጋሪ ደረጃ ሲደርስ:: ሁኔታውን የታዘቡ እስራኤል፥ ለሚን አሜሪካና ሌላ ሀገር ባሉ ኢትዮጵያውያን ምእመናን ባሰባሰቡት ገንዘብ ላይ የገዳማቱ አስተዳደር ጨምሮበት ሰ2004 እ.አ.አ. ታክመዋል::

እስከታከሙ ድረስ የሚቀመጡት ከዴርሡልጣን ወደ ጎልጎታ መተላለፊያ በርና የእስም ክርስቲያን መተላለፊያ ቦታ ላይ ስለነበረ ህመማቸው በአጠገባቸው ለሚያልፍ ሰው ያስታውቅ ስለነበር ችግር ፈጥሮ ነበር::

አረብና እስራኤል ለስንዝር መሬት ደም ሲፋሰሱ ኢትዮጵያውያን ንብረቶቻቸውን እንደዚህ ችላ ማለታቸውና በገዳማቱ ውስጥ ያለው ያስተዳደር ችግር የውጪ ሀገር ዜጎችንም አስገርሟል::

ይሄ ሁሉ ሲሆን የኢትዮጵያ ኤምባሲ የት ነው ያለው?

ይሄ የብዙዎቹ እስራኤል ሀገር ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያንና ከኢትዮጵያውያን ጋር የተያያዘ ጉዳይ የሚሰሩ የውጭ ሀገር ዜጎች ጥያቄ ነው::

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚኖርባት፥ የኢትዮጵያ አብያተ-ክርስቲያናትና የኢትዮጵያ ንብረቶች ባሉባት በኢየሩሳሌም ባይሆንም፣ የኢትዮጵያ ኤምባሲ እስራኤል ውስጥ በቴልአቪቭ ከተማ ውስጥ አለ::

ቴልአቪቭ ከተማ የሆነበት ምክንያት:: በፍልስጥኤምና በእስራኤል መሀል ባለው ችግር በተያያዘ ነው::

ይሄ ኢትዮጵያ ብቻ ያደረገችው ሳይሆን:: የእስራኤል ዋና አጋር-ዩናይትድ ስቴትስ (አሜሪካ) ጨምሮ ሌሎች ከእስራኤል ጋር ግንኙነት ያላቸው ሀገሮች በሙሉ ናቸው::

ኤምባሰ. ጽ/ቤታቸውን ኢየሩሳሌም ያደረጉ ኮስታሪከና ኤልሳልቫዶር ብቻ ናቸው::



የአሜሪካ ምክር ቤት የአሜሪካ ኤምባሲ ከቴልአቪቭ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲዛወር ቢወስንም፣ የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች የነበሩት ቢልክሊንተንና ጆርጅ ቡሽ በፍልስጥኤምና በእስራኤል መሀል ስለ ኢየሩሳሌም ሊካሄድ ስለሚታሰበው የመጨረሻ ስምምነት ያዛባል በማለትና ለአሜሪካ ብሔራዊ ጥቅም አይበጅም በማለት አዘግይተውታል:: ነገር ግን እንደ አብዛኛዎቹ ሀገሮች የቆንስላ ጽሕፈት ቤት [Consulate] (ያውም ሁለት) ኢየሩሳሌም ውስጥ አሜሪካ አላት::

እስራኤል ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ኢየሩሳሌም ስለሆኑ፣ በርካታ ክትትል የሚፈልጉ የኢትዮጵያ ንብረቶችና አብያተ ክርስቲያናት ኢየሩሳሌም ስለ አሉና በሌሎችም ምክንያቶች የኢትዮጵያን ኤምባሲ ወደ ኢየሩሳሌም ለማዛወር ታስባላችሁ ብለን በእስራኤል የኢትዮጵያን አምባሳደር ክቡር አቶ ነጋሽ ክብረትን በሰኔ 2004 እ.አ.አ. ለጠየቅናቸው ጥያቄ?

የአምባሳደሩ መልስ፡- *የእስራኤል ባለስልጣኖች ኢየሩሳሌም ነው የሚገኙት:: ከዚህ ወደ ኢየሩሳሌም ለመመላለስ በየቀኑ ለነዳጅ የምናወጣው ራሱ ቀላል አይደለም:: እኛ ቴልአቪቭ መሆን ስለፈለግን አይደለም እዚህ ያለነው:: እዚህ ለኪራይ ገንዘብ ከምናወጣ ኢየሩሳሌም ውስጥ የኢትዮጵያ ሕንፃዎች ውስጥ ብንሆን ይሻለናል::*

*የኢትዮጵያ ኢምባሲ ቴልአቪቭ የሆነበት ምክንያት ኢትዮጵያ አለም አቀፍ ህጎችን ስለምታከብር ነው:: በተጨማሪ ኤምባሲውን ወደ ኢየሩሳሌም ማዛወር የፓለቲክ ውሳኔ ነው ብለውናል::*

*ንብረቶቹንም በተመለከተ ለሚመለከተው ለመጋቢውና የገዳማቱና የመንግስት ንብረት ጉዳይ ፈጻሚ ጽሐፈት ቤት ሀላፊው ንገሩ:: ስለ ገዳማቱም ይሰማል ስላላችሁት ትችት ለሊቀጳጳስ ንገሩ ብለውናል::*

ከመጋቢውና ከንብረት ጉዳይ ፈጻሚ ጽሕፈት ቤት ሀላፊው በተጨማሪ ኤምባሲው እገዛ የማድረግ ሀላፊነት የለበትም? ስንላቸው::

*የኤምባሲው ዋና አላማ የሚያተኩረው በሁለቱ ሀገሮች መሃል ያለውን የኢኮኖሚ፥ ማህበራዊና ፓለቲካዊ ግኑኙነት ማሻሻል ላይ ነው። የሚል መልስ ነው የሰጡን።*

ሁለተኛ ጥያቄ- በኢትዮጵያና በእስራኤል መሀል ይሄንን ያህል ግንኙነት እያለ የጄሩሡልጣን ችግር በተለይ ጄሩሡልጣን ውስጥ ያሉት የሚካኤልና አርዕባቱ እንሳስት ቤተክርስቲያን እየፈረሱና ጄሩሡልጣን ላይ የፍሳሽ መተላለፊያ ቱቦ ሽታ እየፈጠረ እንዴት ማስተካከል አልተቻለም ብለን ለጠየቅናቸው?

*እኔ ራሴ እንደመጣሁ አብዛኛውን ጊዜዬን ያጠፋሁት እሱኑ ስከታተል ነው። አሁንም እየተከታተልኩ ነው። ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ለጉብኝት መጥተው በነበሩበት ጊዜና ያለፈው ሳምንት ጠቅላይ ሚኒስትሩ መጥተው በነበሩበት ጊዜ የሚመለከታቸውን የእስራኤል ሀላፊዎች አነጋግረዋል። ጥረት እየተደረገ ነው። መንግስት ጥረት አላደረገም ብላችሁ አትፃፉ ነበር መልሳቸው።*

የኢትዮጵያ ኤምባሲ ድምፅ በጠፋበት በኢየሩሳሌም። የተለያዩ ችግሮች ሲደርስ ኢትዮጵያውያንን በመተባበርና በተግባቢነታቸው የተነሳ "ቆንሲል" በማለት ኢትዮጵያውያን የሚጠሯቸውንና ***በኢትዮጵያ ውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ስር የገዳማቱና የመንግስት ንብረት ጉዳይ ፈጻሚ ጽሕፈት ቤት ሃላፊን፤*** ስለሚኖሩበትና ስለሚሰሩበት ስለዘውዲቱ ሕንፃ እንዲህ መነሳቆልና የክፍሎች በቁልፍ መያዝ በሚያዝያ 2004 እ.ኢ.አ. ጠይቀናቸው እንዲህ ብለውናል፡-

*ሕንፃውን ሙሉ ለሙሉ ለማደስ ከፍተኛ ወጪ ያስወጣል። እንዲሁም ልናድስ ስንሞክር ባለቁልፎች ተቃውመዋል ብለውናል።*

*በተጨማሪ እሳቸው ከመጡ በኋላ አስራ አንድ ክፍሎች እንዳስለቀቁና አሁን የሚቀሩት አምስት ብቻ እንደሆኑና እነኛንም ለማስመለስ ጥረት እንደሚያደርጉ ገልፀዋል።*

በእሳቸው ሀላፊነት ስር እያለ የንግሥተ ዘውዲቱ መታሰቢያ ሕንፃ ውስጥ አፓርትመንት ተከራይቶ በርካታ አመታት የቆየ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በ2002 እ.እ.አ ሲለቅ። ለግለሰብ ከሚሸጥ ይልቅ



እሳቸው ለሚመሩት ጽሕፈት ቤት መሸጥ አማራጭ ነበረው። እሳቸው ለሚመሩት ጽሕፈት ቤት መሸጥ እማራጭ ነበረው። በመጨረሻ ግን የገዛው የውጪ ሀገር ዜጋ የሆነ ግለሰብ ነው። ለምን መንግስትን ወክለው እሳቸው ከግለሰቡ ላይ እንዳልገዙትና የተያዙት ክፍሎች ቀስ በቀስ ወደ ኢትዮጵያ አይመለሱም ብለን ስንጠይቃቸው።

*በአገሪቱ ሕግ መሰረት ግለሰቡ የመሸጥ መብት እንዳለውና የተሻለ ክፍያ ስላገኘ አሁን ለገዛው ግለሰብ ሸጠው ብለዋል።*

የገዳማቱ አስተዳደር አባል የሆኑ መነኩሴ በበኩላቸው ይህንን አስተያየት የሚቃረን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡-

*የንብረት ጉዳይ ፈጻሚ ጽሕፈት ቤት የገዳሙን አስተዳደር ወይም መንግስትን ጠይቆ ቢሆን ኖሮ ምንም ቢሆን ከገዛው ባእድ ግለሰብ የተሻለ ገንዘብ ለሻጩ ተሰጥቶት፤ ቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት ሆኖ ይቀር ነበር። በዚያ ላይ ሻጩ ግለሰብ ቀድሞ የንብረት ጉዳይ ፈጻሚ ጽፈት ቤት ሰራተኛ ስለ ነበሩ፤ ኢትዮጵያን እያስተዋወቀ ያለው ሕንፃ ክፍሎች ባዕድ አይገዛቸውም ነበር ብለዋል።*



ኢየሩሳሌም የነቢያት መንገድ ቁ.38/40 የሚገኘው የኢትዮጵያ የንግሥተ ዘውዲቱ መታሰቢያ ሕንፃ በጎን በኩል።

ከሚታየው የንግሥተ ዘውዲቱ ሕንፃ ፊት ለፊት ያሉት የእሥራኤል የትምህርት ሚንስቴር ዋና መስሪያ ቤትና የመርሰዲስ ቤንዝ ቢሮ።








እስራኤል ውስጥ ያሉና እነኚህን ቦታዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው፡- አንደኛ ከእነዚህ ንብረቶችና ኢየሩሳሌም ካለው ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ርቆ ቴል አቪቭ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሲሆን።

ሁለተኛው እዚያው አበሻ ሰፈር ባለው የንግሥት ዘውዲቱ መታሰቢያ ሕንፃ ውስጥ ያለ፥ በኢትዮጵያ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር እነኚኑ ንብረቶች ለመጠበቅ የተቀመጠ ነገር ግን የተቀመጠበትን የዘውዲቱን ሕንፃ ያልጠበቀና ወስጡ ያሉት ክፍሎች ሲሸጡ ብዙም ያልረዳ፣ ስሙ ***በእስራኤል የኢትዮጵያ ገዳማትና የመንግስት ንብረት ጉዳይ ፈጻሚ ጽሕፈት ቤት*** ነው።

ሶስተኛው የገዳማቱ አስተዳደር ነው።

በእነኚህ ንብረቶች ላይ ያላቸው የሀላፊነት ድርሻ ግልፅ ባለመሆኑና በግል ጉዳይ በተፈጠረ አለመግባባት ሶስቱም ክፍሎች መፍትሄ ለማግኘት ተባብረው አለመስራታቸው የተጎዱት እነኚህ ቅርሶች ናቸው።

እስራኤል ውስጥ ስለአሉት የኢትዮጵያ ቦታዎች ሌላ ያነጋገርነው- እስራኤል ውስጥ ... በኢትዮጵያ ታሪክ ከታወቁት ሰዎች አንዱ የሆኑት እና በመካከለኛው ምስራቅ ታሪክ በቴልአቪቭ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌስር የሆኑትን እስራኤላዊውን *ሃጋይ ኤርሊክ* ነው።

በኢትዮጵያውያኖች ፎቶግራፎች (በትልቁ የተሰራ የራስ አሉላ አባ ነጋን ፎቶግራፍ ጨምሮ) የተጣበበው የቴል አቪቭ ዩኒቨርስቲ ቢሮአቸው ውስጥ ከተቀበሉን በኋላ፣ ለምን እስራኤል ዴርሡልጣን ያለውን ችግር እንደማታስተካክልና ዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ያለውንና የሥላሴ ገዳምን የከበበውን ፈንጂ ማንሳት የሚያስችል ቴክኖሎጂ እያላት ቦታውን ከፈንጂ እንደማታፀዳው ስንጠይቃቸው የሰጡን መልስ።

*የእስራኤል ክኔሴት አባላት (የካቢኔ አባላት) ብዙ ነገሮች ናቸው ጭንቅላታቸው ውስጥ ያላቸው [ብዙ ስራ አለባቸው ለማለት ነው]፣ ስለ ዴርሡልጣንና ዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ያለው የሥላሴ ገዳም አያውቁም ብዬ ነው የማስበው። ስለ እነዚህ ቦታዎች የሚያውቁ ከሆነ እወራረዳችኋለሁ ነው ያሉን።*

*የምንችል አይመስለንምና አንስራ ብለን ጠይቀን መልስ አልሰጡንም የሚሉ መልሶች ናቸው የሰጡን::*

የገዳማቱ ማህበር አስተዳደር አባል የሆኑትና በተለይ ይህ ጉዳይ የሚመለከታቸውን በወቅቱ ዋናው መጋቢ የነበሩትን አባት ለምን ሕንፃዎቹ እንደማይጠገኑና ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችን በክፍያም ሆነ በትብብር እንዲሰሩ አታደርጉም ብለን በ2003 እ.አ.አ. ለጠይቀናቸው ጥያቄ፤ የሳቸው መልስ- *የገዳማቱ አስተዳደር ገንዘብ የለውም ነው::*

ነገር ግን በቁልፍ የተያዙትና ኢያሪኮ፥ ቢታንያና ቤተልሔም ያለቱ እንኳን ቢቀሩ:: አበሻ ሰፈር ያሉ ከሀያ በላይ የተከራዩ ሕንፃዎች የሚገኝ ገቢ ስልሳ አምስት መነኮሳት አስተዳድሮ (ኢያሪኮ-2፥ ቤተልሔም-3፥ ቢታንያ-10፥ ኢየሩሳሌምዴርሡልጣን-20፥ ኢየሩሳሌም-ደብረገነት-30) በሚተርፈው ገንዘብ፣ ሕንጻዎቹን ለማደስ የገዳማቱ አስተዳደር ገንዘብ የለውም ማለት፣ በየአጋጣሚው የሚገለፁት ብክነቶች እንዳሉ ያጠናክራል::

እንዲሁም የገዳማቱ ማህበር የአስተዳደር ችግር እንዳስበትና ባለሙያዎች እንደሚያስፈልገው ያሳያል::

ሌላው አማራጭ መፍትሄ:- ከኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችና መንግስት ክትትል በተጨማሪ የገዳማቱ አስተዳደር ላይ የቀጥታ ስልጣን ያለውና ለውጥ የማምጣት አቅም ያለው የፓትርያርኩ መንበርና ሲኖዶስ ነው::

እንደተለመደው ከኢየሩሳሌም ገዳማት አስተዳደር የሚተላለፈውን አመታዊ ሪፖርት ከመስማትና ችግሮች ሲደርሱ የሲኖዶስ አባል ከሚያደርጉት ጉብኝት በተጨማሪ፣ አሁን ያለውን ችግር ባለሙያዎችን አስጠንቶ ከሕንፃዎቹ ከሚገኙ ገቢ ላይ ከቤተክህነት፥ ከመንግስትና ክውጪና ከሀገር ውስጥ ባሉ ምእመናን ልገሳ አሁኑኑ ሁኔታዎች ከቁጥጥር ሳይወጡ እነዚህ ቅርሶች እንዳይጠፉ ማሳደስ፣ ሀላፊነትን መወጣትና ለጋሹ ምእመን ለገዳማቱ የለገሳቸው ንብረቶች ተገቢውን ጥበቃ እንዳጡ ተመልክቶ እጁን እንዳይሰበስብ ይረዳል:: ለምሳሌ በቅርቡ እንኳን በ2003 እ.አ.አ. በእስራኤል ላሉ ገዳማት ማህበር ከአሜሪካ (ከዩናይትድ ስቴትስ) ከ250 000 የአሜሪካን ዶላር በላይ ተዋጥቶ ተልኳል::



በተጨማሪ መንግስት አሁን ያሉትን የገዳማቱን ችግሮች እያያዘ አይቶ፤ ቀድሞ እንደነበረው እነዚህን ንብረቶች በመንግስት ስር እንዲሆኑና በእስራኤል ሀገር ያሉት ገዳማት በመንግስት በጀት እንዲተዳደሩ ለመወሰን ሊገደድ ይችላል::

ይህ ደገሞ ከአሁኑ ጋር ሲተያይ አነስተኛ በጀት ሊሆን ሲችል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ለውጥ ሲደርስ የገዳማቱም ሕልውና አብሮ ሊለዋወጥና አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል::

*ከእነኚህ ሕንፃዎቹ የሚገኘው ገቢ የመንግስት እጅ ከገባ በኋላ በየአመቱ የሚሰጠው መደበኛ 12000 ብር ቀርቶ፤ የገዳማቱ አስተዳደር እራሱ ሕንፃዎቹን አስተዳድሮ ገቢያቸውን በቀጥታ እንዲጠቀም ብፁዕ አቡነ ማትያስ (አራተኛው የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ) ሲጠይቁ:: አፄ ኃይለ ሥላሴ ሕንፃዎቹን ማስተዳደር ይከብዳችኋል ብለው ከተቃወሙ በኋላ፤ በአቡነ ማትያስ አጥብቆ መጠየቅ እንደተፈቀደ:: አባ አብረሃም ባይሩ አጫውተውናል::*

ባጭሩ- ለወገን ደንታ የነበራቸውና መንፈስ ጠንካራ የነበሩ ነገስታት፣ የሀይማኖት አባቶች እና ግለሰቦች አበርክተዋቸው ያለፉት ቅርሶችና የገዳማቱ መተዳደሪያዎች ከመጥፋታቸው በፊት ለማስተካከል ወደፊት ሊገኝ የማይችል እድል አሁን ነው::

“የዴርሡልጣን ችግር ያለውን የጊዜ ርዝመትና ውስብስብነት የተመለከተ ታዛቢ፤ መፍትሄ የሌለው ችግር አድርጎ ያስባል፡፡ ነገር ግን ልብ ብሎ ለተመለከተው መፍትሄ መጥፋት ሳይሆን በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በተለይ የሕግና የዲፕሎማሲ ባለሙያዎችና በመንግሥት መፍትሄ ለመፈለግ በቂ ጥረት እንዳልተደረገና የተደረጉትም ጥረቶች በዘዴና በቀጣይነት እንዳልተደረጉ ይረዳል፡፡ በዚህም የተነሳ ችግሩ እየከፋ ያለ ቢሆንም፤ በአሁን ሰአት ለዴርሡልጣን ችግር መፍትሄ ለማግኘት ጥሩ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ”



“ከአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እስከ አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በነበረው ጊዜ በቅድስት ሀገር በሚገኙት የኢትዮጵያ ገዳማት የደረሰውን ችግር በመመልከትና በዚያም ምክንያት በተወሰዱት ቦታዎች በመቆጨት፤ ከኢትዮጵያ እርዳታ እስከሚመጣ ከሚጠብቁ እዚያው ቅድስት ሀገር ውስጥ ቋሚ የሆኑ መተዳደሪያ ንብረቶች እንዲኖራቸው በማለት አርቆ አስተዋይና ለወገን ደንታ በነበራቸው ነገስታት፥ ግለሰቦችና የሀይማኖት አባቶች የተሰሩ ከኢየሩሳሌም እስከ ኢያሪኮ ያሉ ቦታዎች የቀድሞዎቹ ከጠፉባቸው የተለዩ ምክንያቶች ቢሆንም እንደቀድሞዎቹ ሊጠፉ ነው፡፡”